# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 241 ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# የፌዴራል ፖሊስ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ወንጀሎችን በማክሸፍ ግዳጁን እየተወጣ እንደሚገኝ ገለጸ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ:- ዓለም አቀፍ እና ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂዎች በመታጠቅ እና በመጠቀም የተለያዩ ወንጀሎችን እያከሸፈና ፖሊሳዊ ግዳጁን በመወጣት አፈጻጸሙ በላቀ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እና የፌዴራል ፖሊስ ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መስፍን አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ፖሊስ ከለውጡ ወዲህ ዓለም አቀፍ እና ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የተለያዩ ወንጀሎችን እያከሸፈና ግዳጁን እየተወጣ ይገኛል።

የፌዴራል ፖሊስ በአሁኑ ወቅት ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ እና ዘመናዊ ፖሊሳዊ ትጥቆች ባለቤት መሆኑንና ዓለም አቀፍ ቴክኖሎጂዎችን በመታጠቅና በመጠቀም በርካታ ወንጀሎችን እያከሸፈና ፖሊሳዊ ግዳጁን እየተወጣ መሆኑን በአገር አቀፍ ደረጃ ማናቸውም ሥፍራዎች የሚከናወን ሁነትን በፀጥታ አስተማማኝ ለማድረግና አጠቃላይ ሁነቱን በቴክኖሎጂ ከማዕከል ሆኖ መከታተል እና ማናቸውንም አደጋዎችን መቀልበስ የሚያስችል አቅም መፈጠሩን አብራርተዋል።

የቱሪዝም መዳረሻዎችን፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን፣ ትልልቅ ተቋማት፣ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች የሚበራከትባቸው ስፍራዎች፣ ሜጋ ፕሮጀክቶችና መሰረተ ልማቶችንም በቴክኖሎጂ የታገዘ ጥበቃ እየተደረገ ሲሆን፤ የበለጠ ለማጠናከር አስፈላጊው ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛል። ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን የመታጠቅ ሂደቱ ይቀጥላል ብለዋል።


ፎቶ - ሳሙኤል ተስፋዬ

ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መስፍን አበበ

የሀገርን ሰላም ለማደፍረስ የሚጥሩ አካላት መኖራቸውን ያስታወሱት ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መስፍን፤ ፖሊስ ይህን በሚገባ እያከሸፈ መሆኑን አብራርተዋል።

የፌዴራል ፖሊስ የሪፎርም ሥራዎችን በሰፊው ሲያከናውን መቆየቱንም ጠቁመው፤ ቀደም ሲል የነበሩ

የፌዴራል ፖሊስ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# "በመሬት ዝውውር አንዳንድ አመራሮችና ባለሙያዎች ደላላ ሆነው የተገኙበት ጊዜ አለ"

- ወይዘሮ ሂክማ ከይረዲን
በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ አስተዳደር
የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሃብት ልማት ቢሮ ኃላፊ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ:- ሙስና በተንሰራፋበት የመሬት ዝውውር ጉዳይ አንዳንድ የአስተዳደሩ አመራሮችና ባለሙያዎች ደላላ ሆነው የተገኙበት ጊዜ አለ ሲሉ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሃብት ልማት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሂክማ ከይረዲን ተናገሩ።

ወይዘሮ ሂክማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመሬት ጉዳይ ብልሹ አሰራሮች በከተማው ተስፋፍቷል፣ በተለይ ደላላ የበዛበትና ለሙስና የተጋለጠ የመሬት ዝውውር ስርዓት በከተማዋ ታይቷል።

አንዳንድ የከተማ አስተዳደሩ አመራሮችና ባለሙያዎች ከባለሃብት ጋር በመመሳጠር መሬትን በህገወጥ መንገድ ለማስተላለፍ የሚደረጉ ሙከራዎች በተደጋጋሚ መታየታቸውን ተናግረዋል።

በመረጃ በተደገፈ ሁኔታ የተያዙ አመራሮችና ባለሙያዎች ወደሕግ እንዲቀርቡ መደረጉንም ገልጸዋል። የመሬት አገልግሎትን በተመለከተ በቀጣይነት ሁለት አይነት አሰራር እንደሚተገበርም ጠቁመዋል።

መሬትን ዲጂታላይዝ በማድረግ የግልጸኝነት አሰራርን ማስፈንና የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱን በማጠናከር ሕዝብ እያንዳንዱን መረጃ እንዲያገኝ ማድረግ የትግበራው



አካል መሆኑንም ነው የገለጹት። መሬት ለሌላ አካል የሚተላለፍበት መንገድ ህዝብን እንዲያሳትፍ አቅጣጫ መቀመጡንም አመልክተዋል።

የተወሰኑ አካላት በሞኖፖል የሚይዙት የመሬት አስተዳደር ስርዓት አይኖርም። ሁሉን ያሳተፈና ተጠቃሚ የሚያደርግ መዲናዋን በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መንገዶች ሊጠቅሙ በሚችሉ መስኮች ላይ የመሬት ማስተላለፍ ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ ይጠበቅብናል ብለዋል።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ማንም ገንዘብ ስላለው ብቻ ተነስቶ መሬት ከከተማ አስተዳደሩ በሊዝም ሆነ በጨረታ የሚወሰድበትን አሰራር ሳይሆን፤ የትኛው ቦታ ላይ የትኛው አገልግሎትና ኢንቨስትመንት እንደሚያስፈልግ፣ ይበልጥ ለህዝብ ጠቃሚ የሆነውን አካሄድ በመከተል መሬት የማስተላለፍ ሂደትን እንከተላለን።

ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮቻችንን ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የተደገፉ የክትትልና የቁጥጥር አማራጮችን እናሰፋለን፣ ግልጽና ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ አሰራሮችን በማስተዋወቅም የመሬትን ጉዳይ ስርዓት ለማስያዝ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን ሲሉም ተናግረዋል።

መሬት በህግና ስርዓቱ መሰረት ማስተላለፍ የሚያስችልና ባግባቡ በመመራት ባለሃብቱ ኢንቨስትመንቱን እንዲያከናውን የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል።

«በመሬት ዝውውር አንዳንድ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# "በጋራ ጉዳዮች ላይ በመነጋገር ጠንካራ ሀገረ መንግሥት ለመፍጠር ሁሉም ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል"

- አቶ ኢብሳ ነገዎ
የኦነግ ሊቀመንበር ፖሊሲ ጉዳዮች አማካሪ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ:- አገርን ወደ ብጥብጥ ከሚወስዱ ድርጊቶች እና ተግባራት በመቆጠብ በአገር ሰላምና ደህንነት ሁሉም የድርሻውን በማበርከትና በጋራ ጉዳዮች ላይ በመነጋገር ጠንካራ ሀገረ መንግሥት ለመፍጠር ሁሉም ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ ተገለጸ።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ሊቀመንበር ፖሊሲ ጉዳዮች አማካሪ አቶ ኢብሳ ነገዎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በጋራ ጉዳዮች ላይ በመነጋገር ጠንካራ ሀገረ መንግሥት መፍጠር ያስፈልጋል።

በሀገር ሰላምና ደህንነት ጉዳዮች ላይ ሁሉም አካላት

"በጋራ ጉዳዮች ላይ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






አገሬ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ..

ገጽ 7

"መጻሕፍትን ለተቋማት መለገስ እውቀትን ለትውልድ እንደማስረከብ ይቆጠራል"
- አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ

ገጽ 9

ዜና



ፎቶ - ሔዱስ አብርሃ

ዶክተር አብዱልቃድር አደም

## ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ችግሮች እንዲወገዱና ሰላም እንዲሰፍን ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ ገለጸ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚነሱ ግጭቶች፣ የፍትህ ጥሰቶች፣ የመልካም አስተዳደር መጓደሎችና አለመግባባቶች እንዲወገዱ እና ሰላም እንዲሰፍን ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ የነጻነትና አኩልነትፓርቲ ገለጸ።

የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሊቀመንበር ዶክተር አብዱልቃድር አደም እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚነሱ ችግሮች የመፍትሔ አካል ለመሆን እና ሰላም እንዲሰፍን የሚደረገውን ጥረት በማገዝ የበኩሉን ኃላፊነት ይወጣል።

ዜጎች በሰላም ወጥተው ለመመለሳቸው እርግጠኞች መሆን መቻል አለባቸው። ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት ነው። ልማቱ የሚኖረው፣ ኢኮኖሚውን ማረጋጋት የሚቻለው ሰላም ሲኖር ነው። ሁሉም ቅድሚያ ለሰላም ሰጥቶ መስራት እንደሚጠበቅበትም አመልክተዋል።

ችግሮች በተለያየ አካባቢ ይፈነዳሉ፣ አንዱን እሳት ስናጠፋ ሌላኛው እሳት ይፈጠራል። ይህንን ችግር ለመፍታት የነጻነትና አኩልነት አገራዊ የፖለቲካ ድርጅት ዋነኛ አጀንዳ አድርጎ እየሰራ ነው። ሰላምን ለማምጣት አቅማችን የፈቀደውን ሁሉ ለማድረግ እየሰራን ነው ብለዋል።

ባለፉት አራት ዓመታት ሰላምና መረጋጋት ማምጣት እንዳልተቻለ የገለጹት ዶክተር አብዱልቃድር፤ በአገሪቱ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ሊሰሩበት የሚገባው ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ ነው ብለዋል። ሁሉም ዜጋ በየትኛው አካባቢ ቅድሚያ ለሰላም ሰጥቶ ሊሰራና ሊንቀሳቀስ እንደሚገባም ተናግረዋል።

ሁላችንም ዜጎች በርብርብ ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ጥያቄዎችንና የሥጋት ምንጮችን ማጥፋት ካልቻልን ኢትዮጵያ ከድህነት ተላቅቃ፣ ዜጎች በሰላም፣ በነጻነትና እኩልነት ይኖራሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም ብለዋል ዶክተር አብዱልቃድር።

አባላቶቻችን ግጭት ቀስቃሽ ከሆኑ ድርጊቶች በመራቅ ሰው እንዳይጎዳ እየሰራን ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች በየትኛውም ደረጃ ቅድሚያ ለሰላም በመስጠት አባላቶቻቸውንና ህዝቡን ማስተማር እንዳለባቸውም ዶክተር አብዱልቃድር አመልክተዋል። በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች አባላቶቻቸው ጋር በሚኖሯቸው ግንኙነቶች ቅድሚያ ለሰላም ሰጥተው እየሰሩ እንደሆነም ጠቅሰዋል።

ባለፉት አራት ዓመታት የተፈጠሩ የጸጥታ ችግሮችን ለማርገብ ጥረት ሲያደርጉ እንደነበር የተናገሩት ዶክተር አብዱልቃድር፤ ወደፊትም በመላው አገሪቱ ለአገር ሰላም መስፈን ቅድሚያ ሰጥተው እንደሚሰሩ ተናግረዋል።

የሁሉም ነገር መሰረቱ ሰላም በመሆኑ የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ፣ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም እያንዳንዱ ዜጋ በየትኛውም እንቅስቃሴው ሰላምን ማስቀደም እንዳለበት ዶክተር አብዱልቃድር ተናግረዋል።

ቅድሚያ ለሰላም ትኩረት እንደሚሰጡና በቀጣይም በጎጥ፣ በሰፈር፣ በብሔር፣ በእምነት፣ በአቀማመጥና በሌሎችም ጉዳዮች የሚሽከረከረው የፖለቲካ ብጥብጥ ተወግደው ልማትና ሰላም የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመፍጠር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግም ተናግረዋል።

## ዜጎች በበጎ አድራጎት ተግባር መሰለፋቸው ለሰብዓዊነት ያላቸውን ፅናት እንደሚያሳይ ተገለጸ

**በኃይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፡- ዜጎች በበጎ አድራጎት ተግባር የተሰማሩ የማህበሩ አባላት፣ ሰራተኞችና በጎ ፈቃደኞች የሕይወት መስዋዕትነትን በመክፈል ጭምር ለደግነት እና ለሰብዓዊነት ያላቸውን ፅናት የሚያሳይ መሆኑ ተገለጸ፡፡

የዓለም የቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ቀን በኢትዮጵያ ለ64ኛ ጊዜ ተከብሯል፤ የአዲስ አበባ ቀይ መስቀል ሥራ አስኪያጅ አቶ እስራኤል ገሰሰ እንደገለጹት፤ በሰብዓዊነት ግንባር የተሰለፉ ዜጎች ተግባራቸው ለሰብዓዊነት ያላቸውን ፅናት ያሳያል፡፡

የዓለም ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ቀን በዓል ሲከበር ደግነትን ከሰብዓዊነት ጋር በማስተሳሰር ቅንነትን ለዓለም ለማሳየት ጭምር መሆኑን ጠቁመዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ወገኖችን በሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ምክንያት የእኛን እርዳታ በእጅጉ የሚፈልጉበት ወቅት በመሆኑ ከሌሎች ዓመታት ለየት ያለ መሆኑንም አመልክተዋል።

ለወገኖቻችን በተለያዩ መንገዶች አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም አካባቢን በማጽዳት፣ ደም በመለገስ ለቀይ መስቀል ሰብዓዊ አጋርነትን በተግባር ማሳየት እንደሚገባም ነው ጥሪ ያቀረቡት፡፡

ቀይ መስቀል የሚሰራው በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ ሰዎችን የማገዝ ሥራ ነው የሚሰራው ሀገራችን አሁን ከገጠማት የሰላም እጦት እና ጦርነት ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል የአዲስ አበባ ቀይ መስቀል ቅርንጫፍም በሰብዓዊ ድጋፎች ላይ ተሰማርቶ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የዘንድሮውን በዓል አካባቢያችንን ፅዱና ውብ ለማድረግ እንዲሁም ከአባሎቻችን፣ ከበጎ ፍቃደኞች እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን መልካም ግንኙነት ማጠናከርን ታሳቢ በማድረግ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ቀይ መስቀል የሚሰራቸውን ማናቸውንም ሥራዎች ከልማት ጋር አቀናጅቶ መተግበር ያስፈልጋል፣ በቀጣይ በየሳምንቱ አካባቢን የማጽዳት ተግባር ይኖራል ብለዋል።

ዓለም በአሁኑ ጊዜ ከባድ እና አስፈሪ ክስተቶችን እያስተናገደች ትገኛለች፤ ባለፉት ወራት እና ዓመታት ኮቪድ-19፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ግጭትና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎችና ቀውሶች ተፈራርቀው በርካታ ሰብዓዊ ቀውሶችን አስከትለዋል፤ በአገራችንም ችግሩ ውስብስብ መሆኑን ጠቁመዋል።

ግጭቶች፣ ድርቅ፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ የአንበጣ መንጋ፣ ጎርፍ የመሳሰሉት ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ሳቢያ የበርካቶች ሕይወት ጠፍቷል፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ብዙ ዋጋ ያለው ንብረትም በመውደሙ ምክንያት ሰብዓዊነት የተፈተነበት ወቅት እንደነበርም አስታውሰዋል፡፡

በኢትዮጵያ ለ64ኛ በዓለም ለ75ኛ ጊዜ የሚከበረው የዘንድሮው የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ቀን ‹‹ደግነት ለሰብዓዊነት›› በሚል መሪ ሃሳብ በሁሉም የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች የፅዳት መርሐ ግብር ተካሂዷል፡፡

## ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የቅርስ ቀንን ልታከብር መሆኑ ተገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**



ፎቶ - ሔዱስ አብርሃ

ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው፤

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የቅርስ ቀንን በግንዛቤ ፈጠራና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ልታከብር መሆኑን የቅርስና ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤

እስካሁን ሲከበር የነበረው የሙዚየም ቀን ተብሎ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በአይነትም በርካታ የቅርስ ሀብት ያላት በመሆኑና የቅርስ ቀንን ማክበር ስላለባት ቀኑን ለማክበር ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የተመዘገቡ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት እንደመሆኗ፤ የቅርስ ቀኑን ከማክበር ባሻገር ቅርሶች በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ማህበረሰብ የቅርሶችን ደህንነት እንዲጠበቅ የሚያስችል የግንዛቤ ፈጠራ በመስራት ይከበራል ብለዋል፡፡

ቀኑን ለማክበር በባለስልጣኑ በኩል በዩኔስኮ የተመዘገቡ ቅርሶች የተመዘገቡበትን ቀን በመለየት የግንዛቤ ፈጠራ ለመስራት የኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂ ተነድፎ እንቅስቃሴ መጀመሩንም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

ባለስልጣኑ እስካሁን ደካማ የሆነ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ የነበረው መሆኑን የጠቀሱት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ ጠንካራ ኮሙዩኒኬሽን እንዲኖር በማሰብ በአዲስ መልክ ለማደራጀት ስትራቴጂ ተነድፎ ምክክር እየተደረገበት ነው ብለዋል፡፡

የቅርስ ቀን እንደማንኛውም አገር ማክበር ሳይሆን ግንዛቤ ለመፍጠር ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ የቅርስ ቀን ሲከበር ግንዛቤ የሚፈጥሩ መልዕክቶች ተዘጋጅተው እንዲተላለፉ በማድረግ ቀኑ ይከበራል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታም በርካታ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ከቦታቸው የተወሰዱና የጠፉ በመሆናቸው የሚመለከታቸው አካላት ክትትል እንዲያደርጉ የሚያስችል ሥራ ይሰራበታል ብለዋል፡፡

በቅርስ ጥናትና ጠበቃ ዙሪያ ወቅቱን የመጠነ የኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂ መኖር መቻል አለበት ያሉት ምክትል ዋና ዳሬክተሩ፤ በቅርስ ውድመትና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ አልፎ አልፎ የተሳሳቱና የተዛቡ ግንዛቤዎች በማህበራዊ ሚዲያ ይሰራጫሉ፡፡ እነዚህን ማስተካከልና ትክክለኛ መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ ባለስልጣኑ ጠንካራ ኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂ እንዲኖር እየሰራ ነው፡፡

ዩኔስኮ ቅርሶችን ከመጠበቅ አንጻር አንድ ባለድርሻ አካል ይሆናል እንጂ ዋናው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሆኑ የተመዘገበውን ቅርስ የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ በርካታ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶችን ያስመዘገበች አገር እንደመሆኗ ለቅርሶቿ ደህንነት ቅድሚያ እንዲሰጥ እየተሰራ እንደሚገኝም ረዳት ፕሮፌሰሩ ገልጸዋል፡፡

መቼ እንደሚከበር በቀጣይ እንደሚገለጽ የተናገሩት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ ቀኑ ስለቅርሶች ግንዛቤ ለመፍጠር በትኩረት ይሰራበታል፡፡ ባለስልጣኑ በቀጣይ በእያንዳንዱ ክልል ስለቅርሶች ግንዛቤ በመፍጠር ቀኑን እንዲያከብሩ የማድረግ ውጥን እንዳለው ረዳት ፕሮፌሰር አበባው ገልጸዋል፡፡

# የፋብሪካው ማስፋፊያ በሥራ እድል ፈጠራና በኢኮኖሚ ግንባታ አበርክቶ እንዳለው ተገለጸ

**አዲስ ገረመው**

ደብረ ብርሃን:- ዳሸን ቢራ ፋብሪካ ያሰራው ዘመናዊ የማስፋፊያ ፕሮጀክት የሥራ እድልን በመፍጠር እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማሳደግ አገራዊውን የእድገት ጉዞ ለማሳካት ትልቅ የኢኮኖሚ አበርክቶ እንዳለው ተገለጸ።

ዳሸን ቢራ ፋብሪካ በአንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በደብረብርሃን የሠራውን ዘመናዊ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በተገኙበት ትናንት አስመርቋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የዳሸን ቢራ ፋብሪካ ማስፋፊያ ፕሮጀክትን መርቀው በከፈቱበት ወቅት እንደገለጹት፤ የዳሸን ቢራ ፋብሪካ ማስፋፊያ በሥራ እድል ፈጠራ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በኢኮኖሚ ግንባታ አበርክቶ አለው፡፡

ፋብሪካው ተቋቁሞ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ባሉት ሁለት አሥርት ዓመታት ውስጥ ለውጤት መብቃቱ የፕሮጀክት ተወዳዳሪነቱን በተግባር ያሳየ ነው። ለዘርፉ የሚመጥን የተሟላ ብቃት ያለው እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሁም አገሪቷ የጀመረችውን የልማት ጉዞ ለማሳካት አበርክቶው የላቀ ነው።

ፋብሪካው በአገር ደረጃ እያበረከተ ያለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የጎላ ነው፣ በሥራ እድል ፈጠራና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያ በትኩረት እያከናወነች ላለው ሁለንተናዊ እድገት በጎ ሚና ይጫወታል ሲሉም ጠቅሰዋል።



ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሁለት አሥርት ዓመታት ውስጥ የፕሮጀክት ተወዳዳሪነት ውጤትን በተግባር ማሳየቱንም ጠቁመዋል፡፡

እንደ አገር በሁሉም መስክ ተመጣጣኝ እድገት ለማስመዝገብ መንግሥት በትኩረት እየሰራ እንዳለ በመጠቆም፤ የልማት ሥራውን ከሠላም ማስፈን እኩል ለማስኬድና ውጤት ለማስመዝገብ፣ የህግ የበላይነትንም በማስጠበቅ ረገድ ህዝቡ ከመንግሥት ጎን ሊሰለፍ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የአማራ ክልል የኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪ ወይዘሮ አይናለም ንጉሴ በበኩላቸው፤ ፋብሪካው የሠራው ማስፋፊያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የሥራ እድልና የምርት አቅርቦት ሥራን ያቀላጥፋል ብለዋል።

ፋብሪካው የግብርና ኢንዱስትሪውን ትስስር በማሳለጥ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ገልጸዋል። የግብርና ኢንዱስትሪውን ትስስር በማሳለጥ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረውም ተጠቁሟል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል በበኩላቸው፤ ፋብሪካው አርሶ አደሮች የገብስ ምርትን እንዲያቀርቡና ከውጭ ይገባ የነበረውን የቢራ ብቅል በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት እንደሚያግዝ ተናግረዋል፡፡ ፋብሪካው የውጭ ምንዛሪን በመታደግ ጉልህ ሚና ካላቸው ፋብሪካዎች አንዱ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ለኢንዱስትሪ ምቹ አካባቢ በመፍጠር ኢንቨስትመንትን መሳብ ምን ያህል ምቹ እንደሆነ ዳሸን ቢራ ፋብሪካን በምሳሌነት በማንሳትም፤ ለአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ እድል እና ተጨማሪ የኢኮኖሚ ግብዓት መፍጠር በመቻሉም ምስጋና አቅርበዋል።

ፋብሪካው ሰው ተኮር በሆኑ ተግባራት በርካታ ሥራዎች እያከናወነ ሲሆን፤ በተለይም በትምህርት፣ በጤና፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በግብርና፣ በመሠረተ ልማት፣ በሥራ ፈጠራ፣ በቱሪዝምና መሰል መስኮች በመሳተፍ ከ806 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ ማህበራዊ ኃላፊነቱን መወጣት መቻሉም በመድረኩ ተገልጿል።

ዳሸን ቢራ ፋብሪካ በደብረብርሃን ዘመናዊ የማስፋፊያ ሥራ የምረቃ መርሐ ግብር የፌዴራል እና የክልል ባለስልጣናት፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የቢራ ገብስ አምራች አርሶ አደሮች እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን አካላት በተገኙበት በድምቀት አስመርቋል።

ፋብሪካው ባደረገው ማስፋፊያ ዓመታዊ የማምረት አቅሙ በጎንደርና በደብረ ብርሃን ቅርንጫፉ አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክቶ ሊትር እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።



ፎቶ ጸሐይ ንጉሴ

# "ከዒድ እስከ ዒድ መርሐ ግብር ኢትዮጵያ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ትልቅ ሚና ይኖረዋል"

**- አቶ ኦርዲን በድሪ
የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር**

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሐረር:- ከዒድ እስከ ዒድ ወደ ሀገር ቤት መርሐ ግብር በዓልን ተሰባስቦ ከማክበር ባለፈ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ዋና ዋና የቱሪስት መዳረሻዎች አንዷ ለማድረግ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ ገለጹ።

በሸዋል ዒድ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት አቶ ኦርዲን፤ መርሐ ግብሩ ኢትዮጵያ ያላትን ባሕላዊ፣ ተፈጥሯዊና ታሪካዊ ሀብቶችን ተጠቅማ በአፍሪካ ካሉ ዋና ዋና የቱሪስት መዳረሻዎች አንዷ እንድትሆንና የተያዘውን ሀገራዊ እድገት እውን ለማድረግ የራሱን የጎላ አስተዋጽዖ ሊያበረክት ይችላል ብለዋል።

በተጨማሪም በኢንቨስትመንት፣ በዲፕሎማሲና በሌሎችም መስኮች በሚደረጉ ርብርቦች የውጭና የውስጥ አቅምን ለማቀናጀትና ለማጠናከር የሚያስችል ግንኙነትና ትስስር እንዲፈጠር እንደሚያስችልም አብራርተዋል።

እንደ አቶ ኦርዲን ገለጻ፤ ከዒድ እስከ ዒድ ወደ ሀገር ቤት መርሐ ግብር ከሸዋል ዒድ ጋር ተቀናጅቶ መካሄዱ የሸዋል ዒድ አከባበሩን ከማድመቁ በተጨማሪ በዓሉን በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ለማስመዝገብ የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝና የባሕል፣ የቱሪዝምና የቅርስ ሀብቶችን በመጠበቅና በመንከባከብ ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን ገቢ ለማሳደግ ይረዳል።

የሸዋል ዒድ አከባበር ላይ ለመታደም አጎራባች ሕዝቦችን ጨምሮ ከተለያዩ ክልሎች የሕብረተሰብ ተወካዮች ወደ ሐረር ከተማ መምጣታቸው የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እንዲሁም ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን ለማጠናከር እንደሚያግዝም አስረድተዋል።

የኢፌዴሪ የባሕልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጀላ መርዳሳ በበኩላቸው፥ የሐረሪ ሕዝብ የጥበብና የእውቀት ውጤት ድንበር ተሻግሮ የዓለም ሕዝቦች የቅርስ ሀብት ለመሆን በቅቷል፤ ይህ በምንም ሊተመን የማይችለውን ባሕላዊ እሴት ለመጪው ትውልድ ሳይሸራረፍ መተላለፍ እንደሚኖርበት አጽንዖት ሰጥተዋል።

‹‹ታሪካዊ ቅርሶቻችንና ባሕሎቻችን ቀደምት እናትና አባቶቻችን አቆይተዋል እኛም እሴቶችን በመጨመር ለመጪው ትውልድ ማሸጋገር ይኖርብናል" ያሉት አቶ ቀጀላ፤ ይህ ሊሆን የሚችለው ያሉንን ሀብቶች ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ተጠንተውና ተሰንደው እንክብካቤ ሲደረግላቸው ብቻ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ዘመኑ የሚፈቅደውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ የዚህ ትውልድ ኃላፊነትና ግዴታ ስለሆነ ሀገሪቷ ያሏትን ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶችና ሀብቶች በአግባቡ ተጠብቀው ለመጪው ትውልድ ሊተላለፉ ይገባል።

# የሪፐብሊኩ የቀድሞ ምክትል ፕሬዚዳንት ሌተናል ኮሉኔል ፍስሐ ደስታ የቀብር ሥነ ስርዓት ተፈጸመ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ:- የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ /ኢሕዲሪ/ የቀድሞው ምክትል ፕሬዚዳንት ሌተናል ኮሎኔል ፍስሐ ደስታ የቀብር ሥነ ስርዓት በቅድስት ስላሴ ካቴድራል ትናንት ተፈጸመ።

ሌተናል ኮሎኔል ፍስሐ ሕይወታቸው ያለፈው ዓርብ ሚያዚያ 28 ቀን2014 ዓ. ም. እኩለ ሌሊት አካባቢ ሲሆን፤ የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው ትናንት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል፡፡

ዓድዋ ውስጥ የተወለዱት ሌተናል ኮሎኔል ፍስሐ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በዓድዋ ንግሥተ ሳባ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ አዲግራት ውስጥ በሚገኘው አግአዚ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል።

አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው ኮተቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሩ ሲሆን፤ ወደ ሐረር ጦር ትምህርት ቤት የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ 3ኛ ኮርስ ምሩቅ መኮንን ከሰለጠኑ በኋላ በክብር ዘበኛ ውስጥ ገብተው በንጉሡ ቤተ መንግሥት ውስጥ ተመድበው አገልግለዋል። በደርግ ዘመን በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይም አገልግለዋል። በመጨረሻም የሪፐብሊኩ ምክትል ፕሬዚዳንት መሆናቸው የሚታወስ ነው።

ሌ/ኮሎኔል ፍስሐ ወደ አሜሪካ በመሄድ ከፍተኛ ወታደራዊ ሥልጠና ወስደዋል። ከዚህ ባሻገርም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ተከታትለዋል።

ሌ/ኮሎኔል ፍስሐ ደስታም ለ20 ዓመታት በእስር ካሳለፉ በኋላ ከ10 ዓመት በፊት በይቅርታ መለቀቃቸው ይታወሳል።

ከእስር ከወጡ በኋላ በሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት ስላለፉባቸው ሁኔታዎች የሚተርክ "አብዮቱና ትዝታዬ" የሚል መጽሐፍ ያበረከቱ ሲሆን፣ በዚህም "ደርግ በወሰዳቸው በጎ ዕርምጃዎች እንደምደሰት ሁሉ በማወቅ፣ በድፍረት፣ ባለማወቅና በስህተት ለተፈጸሙት ደግሞ ሙሉ ኃላፊነት በመውሰድ በበኩሌ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እጠይቃለሁ" ብለው ነበር።



ምክትል ፕሬዚዳንት ሌተናል ኮሉኔል ፍስሐ ደስታ

የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ 3ኛ ኮርስ ምሩቅ መኮንን የነበሩት ሌተናል ኮሎኔሉ፥ በደርግ ዘመን በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ አገልግለዋል።

ከደርግ ውድቀት እና ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ለ20 ዓመታት ያህል በእስር የቆዩ ሲሆን፤ ከእስር ከወጡ በኋላም በደርግ ዘመን ስላለፉባቸው ሁኔታዎች የሚተርክ "አብዮቱ እና ትዝታዬ" የሚል መጽሐፍ ፅፈዋል።

ቤተሰቦቻቸው እንደገለፁት ኮሎኔል ፍስሐ የልብ ሕመም የነበረባቸው ሲሆን፤ ህክምናቸውን በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ሲከታተሉ ቆይተዋል።

በቀብር ስነ ስርዓቱ ላይ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክን ጨምሮ የሃይማኖት አባቶች እንዲሁም የቀድሞ የሥራ ባልደረቦች እና ወዳጅ ዘመዶቻቸው ተገኝተዋል፡፡ ሌተናል ኮሎኔል ፍስሐ ባለትዳርና የአንድ ልጅ አባት ነበሩ፡፡

# የአፍሪካ ቀንድ አገሮች የተፈጥሮ ሃብታቸውን በጋራና በትብብር መጠቀም አለባቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ቀንድ አገሮች በቀጣናው ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት በማስፈን ያላቸውን እምቅ የተፈጥሮ ሃብት በጋራና በትብብር መጠቀም እንዳለባቸው የአገራቱ ምሁራን አስገነዘቡ።

“ፒፕል ቱ ፒፕል” በተሰኘ ዓለም አቀፍ ድርጅት አዘጋጅነት የአፍሪካ ቀንድ የጸጥታ ፈተናዎች፣ መልካም እድሎችና አካባቢያዊ ትብብር ላይ ያተኮረ ውይይት በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

በመድረኩ የተገኙት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መስፍን ጣሰው፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ እንዲሁም በዓለም በትብብር በመስራት ያስመዘገባቸውን ስኬቶች አብራርተዋል።

አየር መንገዱ ባለፉት ዓመታት የአየር መንገድ ትስስር አገልግሎት በመስጠት ለአፍሪካ ማህበራዊና ምጣኔሃብት ልማት ከፍተኛ ሚና መጫወቱን ጠቅሰዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

በአሁኑ ወቅት 45 የአፍሪካ አገሮችን በመድረስ አፍሪካን ወደ አንድ ማምጣት የሚለውን መሪ ሃሳብ በመሪነት እየተጫወተ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር የካርጎ፣ የንግድ፣ የቱሪዝም ኮንፈረንስና ለሌሎች ማህበራዊና ምጣኔ ሃብት እንቅስቃሴን በትጋት እንደሚሰራ ጨምረዋል።

የአፍሪካ ቀንድ አገራት ሃብትን በትብብር ከመጠቀም አኳያ ክፍተት እንዳለ ጠቅሰው በአሁኑ ወቅት 80 በመቶ የአፍሪካ ተጓዦች የአፍሪካ ባልሆኑት አየር መንገዶች እንደሚጠቀሙ በማሳያነት አንስተዋል።

በቀጠናው ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት በመፍጠር በትብብርና በጋራ መስራት ከተቻለ ስኬት እንደሚገኝ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተሞክሮ ጥሩ ማሳያ መሆኑን አስረድተዋል።

ከጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳንና ኤርትራ በውይይቱ ለመሳተፍ የመጡ ምሁራን የአፍሪካ ቀንድ የጸጥታ ፈተናዎች፣መልካም እድሎችና አካባቢያዊ ትብብር መስኮችን ዘርዝረዋል።

የአፍሪካ ቀንድ በከፋ ድህነትና ኋላቀርነት፣ በፖለቲካ አለመረጋጋት፣ በእርስ በእርስ ጦርነት፣ መፈናቀል፣ ድርቅ፣ በሽታና ሌሎች ችግሮች ውስጥ መሆኑን ምሁራኑ ዘርዝረዋል።

በደቡብ ሱዳን ጁባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ፣ ሰላምና ጸጥታ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዶክተር አብርሃም ልኡል በአፍሪካ ቀንድ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች ለሰላምና አለመረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ጠቁመዋል።

የጋራ ራዕይና አላማ በመያዝ፣ የተፈጥሮ ሃብቶችን በማልማትና ቀጣናዊ ችግሮችን በትብብር በመፍታት የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እንደሚቻል ያነሱት ደግሞ በኤርትራ የስትራቴጂክ ጥናት ማዕከል ተመራማሪ ዶክተር ፍቅረእየሱስ አምሃ ጺዮን ናቸው።

የጅቡቲ የወደብ አማካሪ ዶክተር መውሊድ አደን፤ በቀጣናው ያሉትን ወጣቶች እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ዋነኛ የልማት አጋር ማድረግ ይገባል ብለዋል።

በአፍሪካ አወንታዊ ውድድርን በማጎልበትና የጋራ ብልጽግናን በማስቀደም ለዜጎቿ የተሻለች አህጉርን መፍጠር መሪዎች ትኩረት ሊሰጡት እንደሚገባም ምሁራኑ ጠቁመዋል።

## የፌዴራል ፖሊስ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ክፍተቶችን በማሟላት በሰው ኃይል ልማት፣ መዋቅር፣ በተልዕኮ አፈፃፀም፣ አደረጃጀትና የፖሊስ አቅምን የሚያሳድጉ አሰራሮችና ስልጠናዎች በዘርፉ ምሁራን ጥናት ተደርጎበት ሰፊ ሥራ መጀመሩን አስገንዝበዋል።

የ10 ዓመት መሪ እቅድ መዘጋጀቱንና አመራርና አባላት የሚመሩበት ሕገ ደንብ መዘጋጀቱን፣ የተልዕኮ አፈፃፀምም በየጊዜው እየተሻሻለ መምጣቱን በቀጣይም ጠንካራ እና ተደራሽ የፖሊስ አገልግሎት እንዲኖር በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ እንደሚገኙም አስረድተዋል።

የፌዴራል ፖሊስ ተቋምም በምስራቅ አፍሪካ አስር ከሚሆኑ ሀገራት ጋር በመቀናጀት በጋራ ጉዳዮች ላይ የሚሰራ ሲሆን፤ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን በመከላከል ውጤታማ ተግባራትን በማከናወን ላይ መሆኑን ተናግረዋል።

ከቀጣናው ሀገራት ጋር በስልጠና የመተሳሰር፣ ለምስራቅ አፍሪካም የፖሊስ የልህቀት ማዕከል ለመሆን ተቋማት እየተገነቡ ይገኛል የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ከሌሎች ሀገራት ጋር ወዳጅነት በመፍጠር በሰፊው በመሥራት ላይ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

193 አገራት አባል የሆኑበት የኢንተር ፖልን በመቀላቀልም በጋራ የትብብር ሥራዎች እንደሚከናወኑ አስገንዝበዋል። ኮሪያ፣ ቻይና፣ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ አውሮፓ ህብረት እና ከመሳሰሉ አገራት ጋር በጋራ ለመሥራት ሥምምነቶች መኖራቸውንና የኢትጵያ ፖሊስ ዓለም አቀፋዊ እውቀትና ክህሎት እንዲላበስ እየተሠራ መሆኑንም ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መስፍን አረጋግጠዋል።

## “በመሬት ዝውውር አንዳንድ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ችግሩን ደረጃ በደረጃ በማስተካከል ውጤት ለማምጣት ይሰራል ያሉት ወይዘሮ ሂክማ፤ ደረጃ በደረጃ ሲባል ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ የሚሄድ እንጂ ከድጡ ወደማጡ የሚባለውን አይነት መሆን የለበትም ብለዋል።

ከመሬት ጋር በተያያዘ ከአገልግሎት አንጻር ሕዝብ በሚጠይቀው መንገድ ፈጣን ምላሽ መሰጠት አለበት፤ በዚህ ረገድ አገልግሎት ሰጪ የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት ችግሮች እንዳሉ ተገንዝበናል ሲሉ ተናግረዋል።

በከተማዋ በእጅ መንሻ፣ በዝምድናና በተለያዩ ህገወጥ አካሄዶች ጉዳዮቻቸው በፍጥነት የሚፈጸምላቸው ሰዎች አሉ። በአንጻሩ ደግሞ ህግን ተከትሎ የሚመጣው ደንበኛ ሲንገላታ ይስተዋላል ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ ሂክማ ገለጻ፤ ችግሩ በተለይ በክፍለ ከተሞችና በወረዳዎች ላይ ሰፊውን ህዝብ ለእንግልት እየዳረገው በመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ አፋጣኝ ማስተካከያዎችን እየወሰደ ይገኛል። እራሱ አመራሩን ወደክፍለከተማዎች ወርዶ እንዲሰራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረትም በየጊዜው ክትትል ይደረጋል።

ልዩ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደትን ተግባራዊ በማድረግ አመራሩ ወርዶ የሚሰራባቸው ክፍለ ከተሞች ይኖራሉ፣ ይህንን አይነት አሰራር በማስፋፋት አመራሩ ህዝብ ጋር ወርዶ በየዕለቱ ችግሮችን እንዲገነዘብና መፍትሄ እንዲያፈላልግ የሚያግዝ አሰራር ይተገበራል ብለዋል ወይዘሮ ሂክማ።

## “በጋራ ጉዳዮች ላይ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ተጠቃሚ በመሆናቸው አገርን ወደ ብጥብጥ ከሚመሩ ተግባራት መቆጠብ ተገቢ መሆኑንም ጠቁመዋል።

መንግሥት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ልሂቃንና ማህበረሰቡ በጋራ ጉዳዮች ላይ በመነጋገር ጠንካራ ሀገረ መንግሥት መፍጠር እንደሚገባ ተናግረዋል።

የአገር ሰላምና እድገት ሊረጋገጥ የሚችለው አገር ስትኖር መሆኑን የጠቆሙት አቶ ኢብሳ፤ በዚህ ረገድ የመንግሥት ድርሻ ጠንካራ መሆን እንዳለበትና የሀገሪቱን የዴሞክራሲ ስርዓት ወደ መሬት ማውረድና የዜጎች ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ ተገቢ ነው ብለዋል።

መንግሥት ህዝብ የሰጠውን አደራ በአግባቡ መወጣት እንደሚገባው እና ህገ መንግሥቱን ማስከበር ላይ መዘናጋት እንደሌለበትም ጠቁመዋል።

የሀገሪቱ ደህንነትና ሰላም ጉዳዮች በሀገር ህልውና ላይ ጥያቄ የሚያጭሩ ከሆነ መንግሥት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። የመንግሥትን ስልጣን በኃይል እቆጣጠራለሁ የሚል አካል ካለም መንገዱ ዝግ መሆኑን ማረጋገጥ ከመንግሥት እንደሚጠበቅ ገልፀዋል።

ህገ መንግሥቱን ለዜጎች በእኩልነት ሥራ ላይ ከማዋል አንፃር የመንግሥት ዋና ተግባር ቢሆንም፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ልሂቃንና ህዝቡ ለተግባራዊነቱ የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባም አቶ ኢብሳ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ለዘመናት በተለያየ የመንግሥት ስርዓቶች ውስጥ ያለፈች ሀገር መሆኗን ጠቁመው፤ በዚህ ሂደት ውስጥም መገፋፋት፣ መጠላለፍና መገዳደል እስከ ቅርብ ጊዜያት ድረስ የሀገሪቱ የፖለቲካ ባህል እንደነበር አስታውሰዋል።

ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ከማሳደግና ለቀጣይ ትውልድ ከማስተላለፍ ይልቅ እርስ በርስ በመጠላለፍ በድህነት እንዲቆዩ ያደረገ በመሆኑ ካለፉ ታሪኮች ሊማሩበት እንደሚገባም መክረዋል።

የሀገር ሰላምና ደህንነት ጉዳይ የመንግሥት ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ፓርቲዎችና የልሂቃን ጉዳይም መሆን አለበት ያሉት አቶ ኢብሳ፤ በህዝብ ድምፅ የመንግሥት ስልጣን መያዝ እንደሚቻል እንጂ ህዝብን በመግደል፣ ንብረትን ማውደምና በህዝቦች መካከል መጠራጠሮች እንዲፈጠሩ አበክሮ መስራት ተገቢ አለመሆኑን ተናግረዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ ልሂቃኖች በአገር ሰላምና ደህንነትን አደጋ ላይ ከሚጥሉ ተግባራት እራሳቸውን በመቆጠብ አንድነትና ሰላሟ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚደረገው ሂደት ሚናቸው መጉላት ይኖርበታል ብለዋል።

ነጻ የሆነ ማህበረሰብ ነፃነት ያላትና ሉአላዊነቷ የተረጋገጠ ሀገር ሊፈጥር እንደሚችል የተናገሩት አቶ ኢብሳ፤ ማህበረሰቡ የአንድን የፖለቲካ ፓርቲ እሳቤ ተቀብሎ ማመንና እሱ ባለው መንገድ ብቻ መጓዝ የለበትም ብለዋል።

ማህበረሰቡ ለበርካታ ዓመታት በጋራ የኖረ፣ የማይነጣጠል ማንነት የፈጠረ በመሆኑ የእርስ በእርስ ቁስሎቻችንን ከመነካካት እንዲያገግም በማድረግ ረገድ ሊሰራበት እንደሚገባ አቶ ኢብሳ ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያን ለሚያሻግሩ የሰላም ሀሳቦች ሁሉም ራሱን ያስገዛ!

አገር ያለ ሕዝብ፤ ሕዝብም ያለ አገር መለያ አልባ ናቸው። ይህ የአገርና ሕዝብ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታነት ግን በሰላም ዋልታነት የተዋቀረ ነው። ምክንያቱም ያለ ሰላም አገር ሊጸና፤ ያለ ሰላም ሕዝብ ሊኖር አይችልምና ነው። ሰላም የሁሉም መሰረት፤ የነገሮች ሁሉ ማጠንጠኛ ሆኖ የሚገለጸውም ለዚሁ ነው።

ይሄን ለመገንዘብ ዛሬ ላይ ከታላቅነት ወደ ፍርስራሽነት የተለወጡ እነ የመን፣ ሊቢያ፣ ሶሪያና ሌሎችም አገራትን መመልከቱ፤ ትናንት የተንደላቀቁና የተቀናጡ ሆነው የሚገለጹትን የእነዚህ አገራት ሕዝቦች አሁናዊ ጉስቁልናና ስደት ማስተዋሉ የሰላምን ከፍ ያለ ዋጋ ብቻ ሳይሆን በምንም አይተኬነት ለመገንዘብ ያስችላል።

ዛሬ ላይ በኢትዮጵያ ያለውና እየሆነ ያለው እውነትም እነዚህን አገራት እንድናስብ፤ ብልህ በሌሎች እየሆነ ካለው የመማሩን ብሂል እንድናሰላስል የሚያስገድደን ሃቅ ሆኗል። ምክንያቱም ዛሬ ላይ በኢትዮጵያ ያለው ተጨባጭ የሰላምና ደህንነት ጉዳይ፤ ያቺ የዘመን ክስተት ሆና ለዓለም ነጻነት እንደ ኮከብ ያበራች አገር ኢትዮጵያን፤ እነዚያ በአሮጌው የዓለም ታሪክ ውስጥ የሚገለጠውን የነጮችን የበላይነት አመድ አድርገው የእኩልነት ታሪክ እንዲጻፍ አዲስ ምዕራፍ የከፈቱ ኃያል ሕዝቦችን፤ ከከፍታቸው ስገነት ሊያወርድ፣ ከምሳሌነት ዙፋናቸው ሊገረስስ እየተውተረተረ ያለ ስለመኖሩ እያስገነዘበን ነው።

በዚህም ዘመናትን በአብሮነት፣ በፍቅር፣ በወንድማማችነትና መደጋገፍ አብረው የዘለቁ፣ አብረው ስለ አገር ሉዓላዊነት፣ ነጻነትና ክብር የተዋደቁ፣ አብረው ክፉና ደጉን ያሳለፉ ሕዝቦችን አንዴ በብሔር፣ ሌላ ጊዜ በሃይማኖት ጥላ ተጠልሎ ለመከፋፈል፣ ለማጋጨትና ለመለያየት በብዙ መልኩ እየተገለጠ ይገኛል። ይህ ደግሞ አንድም በውስጥ ካሉ የተለያዩ ቡድኖች የግል ጥቅምና ፍላጎት የሚመነጭ ሲሆን፤ በሌላ በኩል የኢትዮጵያን ሰላምና አድነት የማይሹ የውጪ ኃይሎች የውጭ የአገር መከታ የሆነውን የኢትዮጵያውያንን ሕብረት ለማላላት የሚያቀነባብሩት ሴራ ውጤት ነው።

ይህ በውስጥ እና የውጪ ኃይሎች ሕብረት የሚፈጸም ሕዝቦችን በማጋጨትና በመለያየት የአገርን የከፍታ ጉዞ የማደናቀፍ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያን እንደ አገር፣ ኢትዮጵያውያንን ደግሞ እንደ ሕዝብ በሚፈልጉት ፍጥነት ተጉዘው በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው መስክ የሚፈልጉት ቦታ እንዳይደርሱ እንቅፋት ሆኖባቸው ይገኛል። ምክንያቱም የፖለቲካው ምህዳር በመጠላለፍና በብሔር እሳቤ ተቃኝቶ እኔነት እንጂ እኛነት እንዳይደመጥ በማድረግ መሳሳብን በመፍጠሩ የፖለቲካ ጉዟችን አድሮ ጥሬ ሆነ። ከመደጋገፍ ይልቅ መገፋፋትን፣ ከመተባበር ይልቅ መለያየትን፣ ከፍቅርና አብሮነት ይልቅ ጠብና ቁርሾን መለያው አደረገ።

በኢኮኖሚውም ቢሆን በጋራ ቆሞና ተባብሮ ሊጋራ ብልጽግና ከመንቀሳቀስ ይልቅ የእኔ ክልል፣ የእኔ ብሔር፣ የእኔ....፣ በሚል ወጥመድ ሃብት ወደ መናጠቅ፣ እንዲሁም የተገነባን ልማት ለማፍረስ መጣደፍ መገለጫው እየሆነ መጣ።

ለዚህ ደግሞ በሰባራ ላይ ሰንጣራ እንዲሉ የፖለቲካ ልሂቃን ነን፣ የፖለቲካ አመራሮች ነን፣ የማህበረሰብ አንቂ ነን፣... ባዮች ፖለቲካው እንዳይረጋጋ፤ ኢኮኖሚው እንዳያንሰራራ ባናት ባናቱ የመለያየት ስብከት፣ የመጨካከንና የመገፋፋት ዲስኩር፣ የመገዳደል አታሞ እያሰሙ ሕዝቡ እንዳይረጋጋ በማድረግ የራሳቸውን የማይበላ እንጀራ መጋገር የዘወትር ተግባራቸው አድርገውታል። ይህ ደግሞ አገር እንደ አገር፤ ሕዝብም እንደ ሕዝብ አደጋ እንዲያንዣብባቸው በር እየከፈተ፤ በሌሎች አገራት የታየው የሕልውና አደጋ እየተቃረበ፤ ሁከትና ጦርነት በየወቅቱ ጎራ እያለ ወዳልተፈለገ ችግር እያመራን ይገኛል።

ይሄን እውነት የተገነዘበው የለውጡ ማግስት መንግስት እና የአገር ተቆርቋሪ ኃይሎች ስለ አገር ሰላም፣ ስለ ሕዝቦች አንድነትና አብሮነት ይበጃል ያሉትን ለማድረግ ጥረት ማድረግ ጀምረዋል። አገራዊ ምክክር በማድረግ ያደሩ ችግሮችን በውይይት በመፍታት የነገዋን ታላቅ አገር እውን ለማድረግ ጉዞው አንድ ብሏል። ይህ እውን እንዲሆንም ስለ አገር ሰላም፣ ስለ ሕዝቦች አብሮነት ያገባኛል የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህ እንዲሆን ያለውን መልካም ሃሳብ ሁሉ እንዲያቀብል ግብዣ ቀርቧል። ይሄን ተከትሎም አገራዊ የምክክር ኮሚሽኑና ኮሚሽነሮቹ ዘርፈ ብዙ ተግባር እያከናወኑም ናቸው።

ይሁን እንጂ ይህ የሚሰምረው፤ የሚፈለገውን ሰላም ማምጣትና የሕዝቦችን አብሮነት በጽኑ መሰረት ላይ ለማኖር አንድ ነገር ይጠበቃል። ሁሉም ለሰላም ቅድሚያ ሰጥቶ የሰላም ሃሳብ ማፍለቅ፤ ኢትዮጵያን ያሻግራሉ ተብለው ለሚለዩ የሰላም ሀሳቦች ራስን ማስገዛት። ይህ ምናልባት ለጥቂቶች ከድንጋይ የከበደ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም እነዚህ ኃይሎች ሕልውናቸው የተመሰረተው በአገር ሰላም ላይ ሳይሆን ሁከትና ግርግር ላይ፤ በሕዝቦች አንድ መሆን ውስጥ ሳይሆን፣ ሕዝቦችን በዘርና ሃይማኖት አቧድኖ በሚፈጠር ግጭትና መፈናቀል ላይ በመሆኑ ነው። ነገር ግን የየትኛውም ቡድንና አካል ጥቅም ከአገር ጥቅም፤ ከአገር ሰላም በላይ አይደለምና ሁሉም አካል ኢትዮጵያን ለሚያሻግሩ የሰላም ሀሳቦች ራሱን ማስገዛት ይጠበቅበታል።

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ለእስካሁኑ ምስጋናችን፤ ለቀጣዩም አደራችን ይድረስ

**በየኔነው ስሻው**

ነዳጅ፣ በኢትዮጵያ ገበያ በየዓመቱ በብዙ ቢሊዩኖች ብር በመንግሥት ድጎማ እየተደረገበት ለተጠቃሚው በቅናሽ ዋጋ እንዲደርስ ሆኖ እስከዛሬ ዘልቋል። በዚህም ከዓለምአቀፉ ገበያ አኳያ ቀጥታ ያለው ዋጋ በሕብረተሰቡ ላይ እንዲያርፍ ቢደረግ ከፍ ያለ የኑሮ ጫና ይፈጥር የነበረበትን ሸክም መንግሥት በራሱ ተሸክሞ ሕዝቡንም አገልግሎት ሰጪውንም ሲደጉም ቆይቷል። ምንም እንኳን መንግሥታዊ ኃላፊነቱን የተወጣ ቢሆንም ለዚህ ተግባሩ ምስጋና ሊቸረው የተገባ ነው።

መንግሥት ነዳጅን በድጎማ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ በሚያደርግባቸው በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ ገበያ በሊትር እስከ 30 ብር የሚሸጠው ነዳጅ ድጎማው ባይኖር ኖሮ ከሰባ ብር ይልቅ እንደነበር የተለያዩ አካላት ሲገልጹ ይደመጣል። ይህ ብቻም አይደለም፤ የኢትዮጵያ የነዳጅ ዋጋ በብዙ መልኩ ከጎረቤት አገራት የነዳጅ ገበያ አኳያ ዝቅ ያለ ሆኖ ቆይቷል። ይህ ሂደት ደግሞ የሕብረተሰቡን የኑሮ ሸክም ከማቃለሉ በተጓዳኝ፤ ነዳጅ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ውጭ ገበያ እንዲቀርብ፤ በግልጽ ቋንቋ የነዳጅ ኮንትሮባንድ እንዲስፋፋ በር የከፈተ ስለመሆኑም ሲገለጽ ቆይቷል።

መንግሥት በከፍተኛ ወጪ እየደጎመ ለሕዝብ ጥቅም የሚያቀርበውን ነዳጅ በዚህ መልኩ በኮንትሮባንድ ወደውጭ ገበያ ማቅረብ ደግሞ በእጅጉ አሳፋሪ እና የሞራል ውድቀት ውጤት ሆኖ የሚገለጽ ነው። መንግሥትም ችግሩን ለማቃለል ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። ሆኖም ችግሩን በሚፈለገው መጠን መከላከል ሳይቻል አሁንም ድረስ ዘልቋል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ደግሞ፤ አሁን ላይ በዓለም ገበያ የነዳጅ ዋጋ ከዕለት እለት እያሻቀበ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በአንድ በኩል የነዳጅ ኮትሮባንድ ንግዱ ሲጧጧፍ፤ በሌላ በኩል መንግሥት ለድጎማ የሚያወጣው ወጪ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ መጣ።

ለአብነት ያህል፤ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከትናንት በስቲያ ይፋ ባደረገው መረጃ፤ በታህሳስ ወር ቤንዚን በሜትሪክ ቶን 870 የአሜሪካን ዶላር እና ናፍጣ በሜትሪክ ቶን 730 የአሜሪካን ዶላር ይሸጥ ከነበረበት ሚያዚያ ወር ላይ ቤንዚን በሜትሪክ ቶን ወደ 1028 የአሜሪካ ዶላር እና ናፍጣ ደግሞ በሜትሪክ ቶን ወደ 1138 የአሜሪካን ዶላር ከፍ ብሏል። በዚህ መልኩ የሚገለጸው የዓለምአቀፍ ገበያ ያለው የዋጋ ጭማሬ እንዳለ ቢታወቅም፤ መንግሥት የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ታሳቢ አድርጎ ከታኅሳስ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ለአራት ወራት ምንም አይነት ጭማሪ ሳያደርግ ቤኒዚኒን በሊትር 31 ብር ከ74 ሳንቲም፣ ናፍጣ ደግሞ በሊትር 28 ብር ከ98 ሳንቲም እንዲሸጥ ወስኖ ቆይቷል።

ይህ እንግዲህ መንግሥት ሕዝቡ ከነዳጅ ዋጋ መጨመር ጋር ተያይዞ ሊፈጠር የሚችለውን የኑሮ ሸክም ለማቃለል ሲል የገባውና የወሰደው ከፍ ያለ ኃላፊነት ነው። ይሄን ሲያደርግ በቢሊዩኖች የሚቆጠሩ ብሮችን ለድጎማ ፈሰስ እያደረገ ነው። ይሁን እንጂ በአንድ በኩል በከፍተኛ ድጎማ የሚገባው ነዳጅ በኮንትሮባንድ ሲቸበቸብ መዋሉ፤ በሌላ በኩል ከጊዜ ወደ ጊዜ በመንግሥት ላይ የሚያርፈው ጫና እያደገ መምጣቱ በኢትዮጵያ ገበያ ላይም በነዳጅ መሸጫ ዋጋ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ስለመሆኑ ሲነገር ቆይቷል። የትናንት በስቲያው የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መግለጫም ይሄንኑ ብሂል እውነት ያደረገ ሆኗል።

በመግለጫው እንደተመላከተውም፤ ላለፉት አራት ወራት የዓለም አቀፍ የነዳጅ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩን ተከትሎ ከሚያዚያ 30 ጀምሮ በነዳጅ መሸጫ ዋጋ ላይ ማስተካከያ አድርጓል። ይሁን እንጂ ይህ ውሳኔ በነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ላይ በወር በአማካይ ወደ ተጠቃሚው መተላለፍ የነበረበት 10 ቢሊዮን ብር ጉድለት እንዲመዘገብና በመንግሥት ላይም ከፍተኛ ጫና ማስከተሉን አስረድቷል። ለምሳሌ፣ በሚያዚያ ወር በዓለም ገበያ ነዳጅ የተገዛበት መሸጫ ዋጋን ታሳቢ በማድረግ ቀጥታ ተሰልቶ ተግባር ላይ ቢውል በአዲስ አበባ ከተማ አንድ ሊትር ናፍጣ መሸጫው 73 ብር እንደዚሁም የአንድ ሊትር ቤንዚን መሸጫ ዋጋ 66 ብር ከ78 ሳንቲም ይሆን ነበር። ሆኖም ሀገሪቱ ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ከዓለም መሸጫ ዋጋ ልዩነትን 85 በመቶ የሚሆነውን ጫና መንግሥት በመሸከም ቀሪውን 15 በመቶ ለተጠቃሚው እንዲተላለፍ በመወሰን የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ላይ መጠነኛ ክለሳ ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል።

በዚህም መሰረት ከሚያዚያ 30 ጀምሮ፣ ለምሳሌ በአዲስ አበባ፣ የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ቤንዚን በሊትር 36 ብር ከ87 ሳንቲም ፣ ነጭ ናፍጣ በሊትር 35 ብር ከ43 ሳንቲም፣ ኬሮሲን በሊትር 35 ብር ከ43 ሳንቲም፣ ቀላል ጥቁር ናፍጣ በሊትር 52 ብር ከ45 ሳንቲም፣ ከባድ ጥቁር ናፍጣ በሊትር 51 ብር ከ78 ሳንቲም እንዲሁም የአውሮፕላን ነዳጅ በሊትር 78 ብር ከ87 ሳንቲም እንዲሆን ተወስኖ ተግባራዊ ተደርጓል።

መንግሥት በዚህ መልኩ 85 በመቶውን ጫና ተሸክሞ 15 በመቶውን ወደተጠቃሚው ማውረዱ መልካም ተግባር ቢሆንም፤ በ15 በመቶውም ቢሆን የተፈጠረችውን የዋጋ ማሻሻያ ተከትሎ በሌሎች ምርትና አገልግሎቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ ሊፈጠር ይችላል የሚል ስጋት ከወዲሁ በህብረተሰቡ ላይ ማደሩ አልቀረም። ህብረተሰቡ ይሄን ቢል ካለፈው የሕይወት ልምዱ ያየውን መሰረት አድርጎ ነውና አይፈረድበትም። ምርትና አገልግሎት አቅራቢዎችም እንኳን ይህችን ያህል ምክንያት አግኝተው ቀርቶ በሉ ሲላቸው ከመሬት ተነስተው ዋጋ ሰማይ ማድረሱን የተካኑበት ነው። ለዚህም ነው ሕዝቡ ከወዲሁ ለእስካሁኑም ሆነ አሁን እየተደረገ ላለው ድጎማና ድጋፍ ከማመስገን ጎን ለጎን፤ አሁናዊ ማሻሻያው በከበደው ኑሮ ላይ ሌላ የኑሮ ጫና የሚፈጥር እዳ ይዛ እንዳትመጣ መንግሥትና ባለድርሻዎችን አደራ የሚለው።

መንግሥትም ቢሆን ይሄን ቀድሞ የተገነዘበው ይመስላል። ምክንያቱም በዋጋ ማሻሻያ መግለጫው ማጠቃለያ ላይ ባሰፈረው መልዕክት፤ "ይህንን መጠነኛ የነዳጅ መሸጫ ዋጋ ክለሳን ምክንያት በማድረግ በእቃዎችና አገልግሎቶች ላይ ሰው ሰራሽ እጥረት የሚፈጥሩና በምርቶች ላይ ዋጋን የሚያንሩ ህገወጥ አካላት ላይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል። ለዚህም በየደረጃው ከሚገኘው የመንግሥት መዋቅር ጋር በመሆን የጸጥታ አካላትና ህብረተሰቡ ተገቢውን ትብብር ሊያደርጉ ይገባል፤" ማለቱም ለዚሁ ይመስላል። ይህ መልካም ምልከታ ነው። ሕዝቡም የሚለው ይሄንኑ ነው። በመሆኑም ምስጋናውን ተቀብሎ ከሕዝብ የተሰጠውን የአደራ መልዕክት ወስዶ ኃላፊነትን በወጉ መወጣትም የተገባ ነው።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

# የከተሜዎች የወንዶች የፀጉር አቆራረጥ ፋሽን

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ፀጉርን መሠራትና መዋብ በሴቶች በኩል እንደ ፋሽን እንደሚዘወተር መናገር ለቀባሪው እንደማርዳት ነው። ልዩ ልዩ የፀጉር አሠራር ስልቶችንና ፋሽን ጎልቶ የሚታየው የሴቶች ፀጉር አሠራር ላይ ነው። ነገር ግን እንደ ሴቶቹ የጎላና የሚዘወተር ባይሆንም የወንዶች የፀጉር አቆራረጥ ፋሽኖችንም የከተሜ ወጣቶች ሲከተሉ ይታያሉ።

በ1960ዎቹ መጨረሻ በአገራችን ከተሞች የነበሩ ወጣቶች ጎልማሶች ተማሪዎችና ሠራተኞች አፍሮ እና ጆንትራ የሚባሉ የፀጉር አቆራረጥ ስልቶች ይከተሉ እንደነበር በወቅቱ ከነበሩ ወጣቶች ጎልማሶች ፎቶግራፎች አይተናል፤ የዚያን ዘመን ትውልዶች ሲናገሩም ይሰማል።

እኛ በዘመናችን ያንን የፀጉር ስልት ብንከተል ሰው ሁሉ አራዳ ሳይሆን ወራዳ፣ በአራዳ ቋንቋ ፋራ ወይም ጅላጅል አድርጎ ሊቆጥረን ይችላል። ወንዶች በዘመናችን ፀጉራቸውን በጣም ቢያስረዝሙት የወቅቱ ፋሽን እና ስልት ስላልሆነ ሰውየው ምንሆነ ብለው ሊያስቡም ሊሰጉም ይችላሉ። የታዳጊዎች ቁንጮ የወጣቶች ጎፈሬ የጆግኖች ሹሩባ አሁን ፍሪዝ የምንለው ፋሽን ሆኖ የመጣው መፈረዝ በወንዶች ፀጉር ላይ ይታይ ነበር። የአፋር ወጣቶች እንደ ባህል ፀጉር በመፈረዝ ይታወቃሉ። ቢኒአሚር የሚባለውን የቀድሞ ቱሪዝም ኮሚሽን ፎቶ ያስታውሷል።

የወንዶች ፀጉር አሠራርና አቆራረጥ ምርጫ በከተሜዎች ዘንድ እንደ ሰዎቹ ፍላጎት እና እንደ ዕድሜያቸው የሚወሰን መሆኑን ያነጋገርናቸው የወንዶች ፀጉር አስተካካይ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔር ስብጥርና ብዙሃነት ጋር ሲታይ በአገሪቱ በርካታ የወንዶች ፀጉር አቆራረጥ ስልት እንዳለ ጠቅሰው፣ ይህን ግን የጸጉር አቆራረጥ በገጠር ከሚኖረው የአካባቢው የባህሉ ተከታይ ውጪ ከተሜዎች ሲተገብሩት እምብዛም አይታይም።

ከተሜዎች በፊልም እና በምዕራባውያን ስፖርት ጨዋታዎች ላይ ያዩትን የፀጉር አቆራረጥና አሠራር ስልት ፀጉራቸውን በመቆረጥና በመሠራት እንደ ፋሽን ለማድረግ ይሞክራሉ ይላሉ።

ወጣት በላይ ታደለ በመርካቶ አመዴ ገበያ መታጠፊያ አቅራቢያ ከሚገኘው ከረሜላ ህንፃ አራተኛ ፎቅ በወንዶች የውበት ሳሎን በፀጉር አስተካካይነት ይሠራል። የፀጉር አቆራረጥ እንደሰው ፍላጎት የሚወሰን ነው የሚለው በላይ፣ በተለይ ወጣቶቹ የተለያየ የፀጉር አቆራረጥ ስልቶችን ይመርጣሉ፤ ሙሉ ፍሪዝ ይሁንልኝ የሚሉ ወንዶችም አሉ ሲል ያብራራል። ፍሬንች ስታይል ብለው የሚመጡ አሉ። እንደ ባላቶኒ ዓይነት ይሠራልኝ የሚል አለ፤ ሥራው በእንደዚህ ዓይነት ስልት ነው በብዛት የሚሠራው ባይ ነው።

የፀጉር አቆራረጥ ስልቶችን ከበይነ መረብ ከቴሌግራም ከመሳሰሉት እናያለን የሚለው በላይ፤ እንደ ጭንቅላት አቀማመጣቸው መርጠን ፀጉራቸውን እያስተካከልን እናስውባለን ይላል። ያየነውን የፀጉር አቆራረጥ ስታይል ወይም ስልት እንተገብረዋለን። በኦን ላይንና በቪዲዮ እንደዚሁም በፎቶ እናሳያዋለን ከመረጠውና ከእሱ ጋር የሚሄድ ከሆነ ፀጉሩን እንደፍላጎቱ አስተካክለን እናስውባለን። ፍላጎት እና ምርጫ ካለው ያንን የፀጉር አቆራረጥ ስልት ይቀበላል። እናሳየዋለን ከወደደው አስተካክለን እንሠራለታለን ሲል ያብራራል።

በላይ የፀጉር አቆራረጥ ሥራውን የለመደውና ያዳበረው በልምድ ነው። ሠፈር ውስጥ ጓደኞቹ እርስ በርሳቸው ጸጉር ይቆራረጡ ይስተካከሉም ነበር። አጠገባቸውም ፀጉር ቤት ስለነበር እዛ ልምዱን አግኝቷል፤ በዚህ ሥራ ወደ ስምንት ዓመት እንደሆነው ነው በላይ የሚናገረው።

እንደ በላይ ገለጻ፤ የፀጉር አቆራረጥ ስታይልና ፋሽን የሚከተሉት ቢያንስ ከ18 ዓመት እስከ 35 ዓመት የሚደርሱ ወጣቶች ናቸው። ከ35 ዓመት እና ቢያንስ እስከ 40ዎቹ ዓመት መጨረሻ የሚደርሱት ደግሞ ፍሪዝ ምናምን ወደሚለው ያደላሉ። ከዛ በላይ የሆኑት ደግሞ በብዛት መደበኛ የፀጉር አቆራረጥን ይመርጣሉ።

ሰው በወቅቱ ካለው ነገር ጋራ የሚዛመድ የፀጉር አቆራረጥ ስታይል ይከተላል። በኳስ ጨዋታ በቴሌቪዥን እንዲሁም ፊልም ድራማ የመሳሰሉት ነገሮች ሲመለከት ያንን የፀጉር አቆራረጥ ስልት ለመከተል ወደ እኛ መጥቶ ፀጉሩን ይስተካከላል ሲል ያብራራል።

እንደ በላይ ገለጻ፤ በብዛት በኳስ ጨዋታው አድንቀውት የፀጉር አሠራር ስልቱን የሚከተሉ በፊልም ላይ አይተው የወደዱትን ተዋናይ የፀጉር አቆራረጥ ስልት የሚከተሉ ብዙ ወጣቶች አሉ። አብዛኛዎቹ ግን በኳስ ጨዋታ ላይ ያደነቁትን ተጫዋች የፀጉር አሠራር እና አቆራረጥ ስልት ይከተላሉ።

በፊልም እና በኦን ላይንም አይተው ይሄን ፋሽን ተግብርልኝ ብለው በብዛት ፀጉራቸውን ለመሠራት ወደ ጸጉር ቤቱ እንደሚመጡም ይናገራል። «እኛም እያየን በሙያችን መሠረት እንደወደዱት እናስተካክልላቸዋለን ይላል።

አንዳንዶቹ የሚመርጡት የፀጉር አቆራረጥ ስልት አንዳንዴ ከጭንቅላታቸው ቅርጽ የማይሄድበትም ጊዜ እንዳለ ተናግሮ፣ ምርጫቸው ከራሳቸው ቅርጽ ጋር እንደማይሄድ እናስረዳቸውና ሌላ የአቆራረጥ ስልት እንዲመርጡ እንነግራቸዋለን ሲል ይናገራል። ለቅያሬ በመረጡት መሠረትም ከራሳቸው ቅርጽ ጋር እንዲዛመድ በማድረግ እንደሚያስተካክሏቸው ያብራራል።

በአራት ኪሎ ድንቅ ሥራ ህንፃ ሦስተኛ ፎቅ በአንቴ የወንዶች የውበት ሳሎን የሚሠራው አባይነህ ሽፈራው በፀጉር አስተካካይነት ከአስር ዓመት በላይ ሰርቷል፤ ሙያውን ያዳበረው በልምድ እንደሆነ ይናገራል። ሠፈር ውስጥ ፀጉር ቤት ስለነበረ በዚያ በተደጋጋሚ አስተካካዮቹ ለምሳ ሲወጡ ህፃናትም አዛውንትም ሲመጣ ፀጉር እያስተካከለ እንደለመደ ይገልፃል።

በብዛት ወደ እሱ ፀጉር ለመስተካከል የሚመጡት ወጣቶች እንደሆኑ የሚገልጸው አባይነህ፣ የሚመርጡት ቁርጥ በብዛት ዘመናዊ የሆነ ስልት መሆኑን ይናገራል። በአብዛኛው ፌድ የሚባል የአቆራረጥ ስልት እንደሚከተሉ ይናገራል፤ እሱም ልክ እንደ በላይ ትልልቆቹ መደበኛ የፀጉር አቆራረጥን እንደሚመርጡ ይጠቁማል።

አቆራረጡን ለማዘመን በይነመረብ እና ሌሎችንም በማየት ራሱን እያዳበረ እንደሆነ የሚገልፀው አባይነህ፤ ፀጉራቸውን ለማስተካከል ከሚመጡ ወጣቶች አብዛኞቹ በኳስ ጨዋታ፣ በፊልም፣ በድራማ ላይ በቴሌቪዥን ያዩትን የአቆራረጥ ስልት መርጠው አሳይተውኝ በፍላጎታቸው መሠረት አሰማምርላቸዋለሁ ሲል ያስረዳል። የግድ ባይመስልም በፊልምና በኳስ ላይ ያየሁትን እንደምርጫቸው አስተካክልላቸዋለሁ ባይ ነው።

ጸጉር አስተካካዮቹ ከቀለም ጋር በተያያዘ በብዛት የሚጠቀሙት ለፀጉር ማደግና መለስለስ የሚረዱ እንደ ቫይታሚን የሚያገለግሉ ቀለሞችን ነው። ለእዚህ ስራ አባይነህ እንደ ኮንዲሽነር ዓይነት ቀለምም ተመራጭ ነው፤ ይህም የበለጠ ፀጉሩን ያስውበዋል ያሳምረዋል። ካለው ፋሽን ጋር ደግሞ የበለጠ የሚሄድ እንደሆነም ነው የሚናገረው።

ብዙዎቹ ፀጉር አቆራረጥ የሚመርጡ ወጣቶች የራሳቸው ስልት እንዳላቸው ጠቅሶ፣ ይህንንም በኪስ ስልካቸው ይዘው ጸጉር ቤት እንደሚሄዱ ይናገራል። በዚህ በመረጡት የፀጉር አቆራረጥ ስልት መሠረት እንደሚስተካከልላቸው ነው አባይነህ የሚገልፀው።

በጸጉር አቆራረጥ አሁን ብዙ አማራጭ እንዳለም ገልጾ፣ የሚፈልጉትን የአቆራረጥ ስልት መርጠው ይዘው ለመምጣት ብዙም እንደማይቸገሩም ይናገራል። በግሉ የሚመርጠው የአቆራረጥ ስልት ብዙ እንዳልሆነም ተናግሮ፣ ደንበኛ ሁሌም ትክክል ነው ብሎ በማመን የወደዱትን የአቆራረጥ ስልት እንተገብራለን በማለት ያስረዳል።

# ማረፊያ/ትዝብት

# ጥንቃቄ አይለየን !

**(አቤል ገ/ኪዳን)**

ሰሞኑን ቢቢሲ አማርኛ ስለ ሕወሓት ያልተለመደ ዘገባ ሰርቷል። ሕወሓት ለመዝመት ፈቃደኛ ያልሆኑ ልጆች ወላጆችን እያሰረ መሆኑን ተገለጸ ይላል ዘገባው። ዘገባውን ያልተለመደ ያሰኘው የምእራቡ ሚዲያ እስካሁን ሊቀበለው እና ሊዘግበው ያልፈለገውን ዘገባ መስራቱ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን ዘገባው የሚያመለከተው ሕወሓት አሁንም ለጦርነት ዝግጅት ማድረጉን እንዳላቆመ ነው። እንዲያ ባይሆን ኖሮ አሁን ምልክቶች በሙሉ ለሰላማዊ መፍትሄ እያመለከቱ ባለበት በዚህ ወቅት ልጅ አዋጡ እያሉ ማሰር አስፈላጊ ባልሆነ ነበር። ሕወሓት ለሌላ ዙር ጦርነት ዝግጅት ላይ ነው። አሁንም ወጣቶች እየተመለመሉ ነው። አዛውንቶችም እንዲሁ ለውጊያ እንዲሰለፉ እየተገደዱ ነው። ህዝቡ በሰብአዊ እርዳታ ከሚሰጠው እንጀራ እየጋገረ ለሰራዊቱ እንዲያቀርብ እየተገደደም ይገኛል።

በሌላም በኩል ወደ ትግራይ የሚገባው ሰብአዊ እርዳታ ቁጥር ጨምሯል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ግዙፍ የጭነት መኪኖች ምግብ እና መድህኒት ይዘው ወደ ትግራይ ገብተዋል። እየገቡም ናቸው። እርዳታው ለትግራይ ህዝብ እጅግ አስፈላጊ ነው።

እርዳታው እጅግ አስፈላጊ የሚሆነው ግን በትክክል ለታቀደለት ሰብአዊ አላማ ሲውል ብቻ ነው። አልያም እርዳታው ለትግራይ ታጣቂ ሀይል፣ ለወታደራዊ ዘመቻው በስንቅነት የሚያገለግል ከሆነ ጦርነቱን ከማራዘም እና ከማወሳሰብ ያለፈ ጥቅም አይኖረውም። ስለዚህም የሚጋዘው እርዳታ በእርግጥም ለሰብአዊ እርዳታ የተላከ ነው ? የትግራይ ህዝብስ በታሰበው መልኩ እንዲያገኘው እየተደረገ ነውን? ወይስ ወታደራዊ ስንቅ ነው የሚለውን መለየት ያስፈልጋል።

ሰሞኑን ፋና ብሮድካስቲንግ በቴሌቪዥን ጣቢያው ባቀረበው ዘጋቢ ፊልም ላይ የቀረቡት መረጃዎች በሙሉ የሚያመለክቱት ደግሞ ሕወሓት አሁን በነጠላ ሳይሆን ከሌሎች የሽብር ቡድኖች ጋር በትብብር እየሰራ እንደሆነ ነው። ኦነግ ሸኔ ፤ አልሸባብ ፤ እና ሌሎች ጥቃቅን የሽብር ቡድኖች ከሕወሓት ጋር ግንባር ገጥመው እየሰሩ ነው። ይህ በእርግጥ አዲስ መረጃ አይደለም።

ይህ የሚያመለከተው ግን ሕወሓት አሁንም አላማው አገርን ማተራመስ እንደሆነ እና በዚህ ትርምስ መሀል በምትፈጠረው ቀዳዳ ለመሹለክ ፍላጎት እንዳለው ነው። በእርግጥም ይህ አላማው በተወሰነ መልኩ እየተሳካ ይመስላል። በአንድ ጎን የብሄር በሌላ ጎን የሀይማኖት ትርምስ በየአቅጣጫው እየተፈጠረ ነው። በዚህም መንግስት ጫና ውስጥ ገብቷል።

እነዚህ ሁከት እና ትርምሶች የፌደራሉ መንግስት ሙሉ ትኩረቱን በሕወሓት ላይ ብቻ እንዳያደርግ ለማድረግ የታቀዱ ተግባራት ናቸው። እንዲያም ቢሆን ሕወሓት የፈለገውን መሹለኪያ ቀዳዳ እስካሁን አላገኘም። ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉ ሕወሓት የሚፈልገውን ባያገኝ እንኳ ጥፋት ሊያደርስ ይችላል ብሎ መገመት ይገባል።

ስለዚህም የደህንነት መረጃዎች በአግባቡ ሊሰበሰቡ፤ ሊተነተኑ እና አቅጣጫ ሊቀመጥባቸው ይገባል። ጠበብት እንደሚሉት፤ ለጦርነት ዝግጅት የሚደረገው በሰላሙ ጊዜ ነው። ስለዚህም ከባለፈው ስህተት መማር ያስፈልጋል። በተለይም የጥቅምት 24ቱ ክስተት ብዙ ትምህርት ለሁላችንም ሰጥቶ አልፏል። አይሆንምን ትተን ይሆናልን አስበን መዘጋጀት ግዴታ ነው።

በአደራዳሪዎች በተደጋጋሚ እየተመከርን ያለነው "ፖለቲካዊ መፍትሄ"ም ተጨባጭ ውጤት የሚያመጣው ያንን ማስፈጸም የሚቻልበት ወታደራዊ አቅምም አብሮ ሲኖር ነው። ስለዚህም በሕወሓት በኩል እየተከናወነ ያለውን ዝግጅት አይነት እና መጠን መገንዘብ፤ ያን ለመመከት የሚያስችል አቅም መፈጠሩን ማረጋገጥ፤ ከዚያም ነገሮችን በንቃት እየተከታተሉ ጎን ለጎን ፖለቲካዊ መፍትሄ ማፈላለግ ላይ ማተኮር በተመሳሳይ ሰአት መከናወን የሚገባቸው ስራዎች ናቸው።

እዚህ ጋ አንድ ታሪክ ማስታወስ ይገባል፤ የደርግ እና የሕወሓት ታሪክ። ደርግ እና ሕወሓት 17 አመታት ተዋግተዋል። 17 አመት ሲዋጉ ልክ አሁን እንደነበረው ሕወሓት የትግራይ ህዝብን እንደ መያዣ ተጠቅሞ ይዋጋ ነበር። ረሀብ ዋነኛ መጫወቻ ካርዱ ነበር። እህል እንዳይገባ መንገዶችን በፈንጂ ማጠር ከዚያም ረሀብ እንዲፈጠር ማድረግ ከዚያም የተፈጠረውን ረሀብ ከሰብአዊ ክስተት ወደ ፖለቲካዊ ጉዳይ ማዞር እና ደርግን ጫና ውስጥ መክተት፤ የሚመጣውን እርዳታ መሸጥ እና መሳሪያ መግዛት፤ የቀረውን ደግሞ ለታጋዮች ቀለብ ማዋል ከዚህ ቀደም ሕወሓት በሚገባ የተገበረው እቅድ ነው። በተለይም ከ1977 እስከ 1983 ባለው ጊዜ ይህ ተግባር በሚገባ ተከውኗል።

በዚህ መልኩ ለአመታት የተጓዘ ድርጅት አሁንም ቢሆን ህዝብን እያስራበ በዚህ መልኩ ለመቀጠል ይቸገራል የሚል እምነት ሊኖር አይገባም። የታሪክ መዛግብት እንደሚያስረዱት፤ እንደውም ሕወሓት የተሻለ የትግል ሀይል ሆኖ ደርግን መውጋት የጀመረው ከድርቁ በኋላ በተከሰተው ሁኔታ ተጠቅሞ ነው።

እርግጥ አሁን ላይ ያለው ሁኔታ ከዚያ የሚለይ ብዙ ነገር አለው። ዛሬ ኤርትራ የሕወሓት መደበቂያ ዋሻ አይደለችም። የሱዳን ኮሪደር ዝግ ነው። ከእህል ጋር አብሮ መሳሪያ ማሻገርም አይቻልም። ሌላም ሌላም።

እንዲያም ቢሆን ግን ያን ወቅት እና አሁንን የሚያመሳስሉ ታሪኮች አሉ። ዋነኛው ደግሞ ያኔም ዛሬም የትግራይ ህዝብ ሰብአዊ ሰቆቃ ለሕወሓት ፖለቲካዊ ተልእኮ መጠቀሚያ መሆኑ ነው።

ደርግ ያኔ ስለ ሕወሓት ወታደራዊም ሆነ ፖለቲካዊ አቅም ትክክለኛ ትንታኔ አልሰራም ነበር። ሕወሓትን እንደ ተራ ወንበዴ ነበር የሚያየው። ከሕወሓት ጀርባ ያሉትን ረዣዥም እጆች እና አላማቸውን በሚገባ አላስተዋላቸውም ወይም እንዲሁ ኢምፔሪያሊስት ጠላቶች ብቻ ነበር የደመደማቸው። ወታደራዊው ሀይል የተሰጠው ተልእኮ እና እቅድ በተቃራኒው ሀይል በኩል ቀድሞ ይደርስ ነበር። ሌላም ሌላም። እነዚህ የስሌት ስህተቶች ቀስ በቀስ ተደማምረው መጀመሪያ ሰራዊቱን ከዚያም የፖለቲካ ስርአቱን እንዲፈርስ አድርገዋል።

ይህ ታሪክ አስተማሪ ነው። የስሌት ስህተት ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል የታየበት ስህተት ነው። ስለዚህም ስሌቱ ሲሰራ በጥንቃቄ መሆን አለበት። የሕወሓትን የማድረግ አቅም (capacity) አቃሎ ማየት አደገኛ ነው። ከማድረግ አቅሙ በበለጠ የማድረግ ፍላጎቱም (will) ከፍተኛ እንደሆነ እና ይህ ፍላጎት ደግሞ ንጹሀንን እስከመማገድ እንደሚደርስ መገንዘብ ወሳኝ ነው።

ስለ ድርድር ስላወራ እና ተከታታይ መግለጫዎችን ስላወጣ ሕወሓት የፖለቲካዊ መፍትሄ ፍላጎት ብቻ ነው ያለው ብሎ መገመት ስህተት ነው። ይህ የሚሰበስበው እና የሚያደራጀው ወታደራዊ ሀይልም በድርድሩ ወቅት እንደ መጠቀሚያ ሊያደርገው ብቻ እንጂ በተግባር ሊጠቀመው አይደለም ብሎ ማሰብም አዋጭ አይደለም። ብዙ መቶ ሺ ወጣቶችን የማገደ ሀይል ሌሎች መቶ ሺዎችን ለመጨመር አያንገራግርም።

ጣርማ በር ድረስ በእብደት እየጋለበ የመጣ ሀይል ይህን እብደቱን ለመድገም ሌላ አነሳሽ ምክንያት ያስፈልገዋል ብሎ ማሰብም ሞኝነት ነው። የጥቅምት 24ቱን እብደት ያበዱት ሰዎች አሁንም በቦታቸው አሉ። ስለዚህ ይህን ሀቅ በልብ አድርጎ መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው። ስለዚህም ማየት የምንፈልገውን ብቻ ሳይሆን ሊሆን የሚችለውን ማወቅ እና መዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# አገሬ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ..

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ህይወት ጥያቄ ናት፤ ጠይቆ መልስ ማግኘት ደግሞ የሰውነት ባህሪ ነው። ሰው ካልጠየቀ ጠይቆም መልስ ካላገኘ ረፍት የለውም። በዚህ ረፍት ማጣት ውስጥ ደግሞ የሚከናወኑ አያሌ ርባናቢስ ህይወቶች አሉ። እኚህ ርባና ቢስ ህይወቶች ባለመጠየቅ የሚፈጠሩ የሰውነት ጉድፎች ናቸው። ዛሬ ላይ ጉድፍ ሆነውብን እያሰቃዩን ያሉት አገራዊ ችግሮቻችን ባለመጠየቅ የጸነስናቸው፣ ጠይቀንም መልስ ባለማግኘት የፈጠርናቸው ናቸው። ዛሬ ላይ ችግር እየሆኑብን ያሉ እንከኖቻችን ባለመጠየቅ ከትላንት ወደዛሬ ያመጣናቸው ታሪኮች ናቸው። እኚህ ችግሮቻችን እልባት እንዲያገኙ በጠረጴዛ ዙሪያ መቀመጥና መልስ መፈለግ ያሻናል። ድጋሚ በታሪኮቻችን ላይ ነፍስ እንዳይዘሩ አድርገን በእርቅና በተግባቦት ገለን ልንቀብራቸው ይገባል። ዛሬ ላይ የአባቶቻችን ጥበብ፣ የፊተኞቻችን አስተውሎት የት እንደገባ አላውቅም። እንዳባቶቻችን የሆነ አንድም ነገር እያጣን ነው። እኔነትን ለብሰን፣ እኔነትን ተጎናጽፈን መኖርን እንደ ትልቅ ስልጣኔ በመቁጠር እየተደነቃቀፍን እንገኛለን።

እኛ እኮ ዛሬን አናውቀውም፤ በዛሬ ብርሀን ትላንትን የምንሞቅ ሞኞች ነን። ዛሬ ላይ ሆነን ወደ ትላንት እየሸሸን የነገር ቁርሾ የምንፈልግ፣ ከፉዎች ያስቀመጡልንን የውሸት ሰነድ እየበረበርን ዛሬን የምንገፋፋ መካሪ ያጣን ነፍሶች ነን። ሰው እንዴት አዲስ ታሪክ መጻፍ ያቅተዋል? ሰው እንዴት ወደፊት መሄድ ያቅተዋል? ሰው እንዴት በተሻለ ዘመን ላይ ተፈጥሮ በመነጋገር መግባባት ይሳነዋል? ሰው እንዴት ለጋራ ጥቅም ለአንድነት መተባበር ሲገባው ለመለያት ይበረታል? እኛ እንዲህ ነን። ወርቃችንን በጠጠር የቀየርን፣ እንቁአችንን በፉንድያ የመነዘርን፣ ሰላማችንን ለውሸት የሸጥን ሞኞች። እስከመች እዛው እየረገጥን እንኖራለን? እስከመች እልፍ ማለት ያቅተናል? ኧረ እንቃ!፤ ከእኛ በቀር እኮ በአገሩ ጉዳይ ያንቀላፋ የለም። ሁሉም የአለም አገራት ለጋራ አገራቸው በጋራ እየተጉ ባለበት ሰዐት ላይ የእኛ ማንቀላፋት አልገባ ብሎኛል። አለም በስልጣኔ ቀድሞ፣ በአንድነት በርትቶ የምድር ኑሮ በቃን ብሎ ጨረቃ ላይ ቤቱን እየሰራ ነው። መንግስታት በአንድ ሀሳብ፣ በአንድ ልብ ሊመክሩ አለምን በግሎባላይዜሽን ስም ወደ አንድ ሊያመጣት እየሰሩ ነው። እኛ ግን በገዛ አገራችን ላይ ከገዛ ወንድሞቻችን ጋር መግባባት ተስኖናል፤ ለምን? ራሳችንን እንጠይቅ።

ባለመግባባታችን ራሳችንን ካልሆነ የምንጎዳው ማንም የለም። ባለመስማማት አገራችንን ካልሆነ የምናራቁተው ማንም የለም። ከትላንት እስከዛሬ ባለመግባባት እየተጎዳን ኖረናል። አሁን ግን እንጠይቅ፤ ጠይቀንም መልስ እናግኝ። ለአገር ሰላም፣ ለህዝቦች አንድነት ከእኔ ምን ይጠበቃል ስንል ራሳችን መጠየቅ ግድ ይለናል። ሰላም ተዐምር የለውም፤ የሰላም ተዐምሮች እኛ ነን። ሰላም በእኔና በእናተ በጎ ሀሳብ በኩል ተጸንሶ የሚወለድ፣ ተወልዶም የሚያድግ ነው። ሰላም በእኔና በእናንተ መተቃቀፍ ውስጥ የሚያብብ፣ አብቦም የሚያሸት የነፍስ ናርዶስ ነው። ሰላም በይቅርታና በፍቅር ከትውልድ ትውልድ የሚሻገር የበጎ አእምሮና ልብ ውጤት ነው። የተሸነፍነው እኛው ነን። ራሳችን ለራሳችን መሆን አልቻልንም። ሞኝነታችንን ተመልክተው ሌሎች እንደፈለጉ እያደረጉን ነው። በትንሽ ነገር እያሽከረከሩን ነው። በጣም የሚገርመው ከፉዎች መርዛቸውን የሚረጩብን በተለየ መንገድ ሳይሆን በቀላል መንገድ እኛን በመጠቀም ነው።

ይህ ማለት የእኛን አንድ መሆን የማይፈልጉ ኃይሎች እኛን ለመጉዳት ሩቅ መሄድ ሳይጠበቅባቸው እኛኑ ተጠቅመው እኛኑ ይጎዳሉ ማለት ነው። ይሄ ደግሞ የእኛን ድክመት፣ የእኛን ከሰላም ይልቅ ለነውጥ መቸኮላችንን ያሳያል። አይገርምም ግን ጠላቶቻችን እኛን ለመጉዳት እኛን ሲጠቀሙ? በአለም ታሪክ የሌለ ነገር አገራችን ውስጥ እየተፈጠረ ነው። ጠላት ከሩቅ አይመጣም እንደሚባለው እስከዛሬ በአልሸነፍም ባይነት አገራችንን ስንጎዳ የነበርነው ሌላ ሳይሆን እኛው ነን። እስከዛሬ በአንድነት ወደፊት መሄድ እየቻልን በእኔነት ስሜት ወደ ኋላ መቅረትን የመረጥነው ራሳችን ነን። ኢትዮጵያን አሁን ላለችበት የፖለቲካና የማህበራዊ ቀውስ የከተትናት እኛው ነን። እኛው ለእኛ ጠላቶች ሆነን ኖረናል፡ አሁን ግን ከዚህ አመለካከት መውጣት ይኖርብናል። ለዘመናት የትላንትን ጸሀይ እየሞቅን፣ የአምናን ዶሲ እየበረበርን ኖረናል። ለአመታት በአንድ አይነት የፖለቲካ አስተሳሰብ አንድ

> **አገር ፍቅር ሲርቃት፣ አንድነት ስታጣ ሶርያን ናት። ህዝብ ጥላቻና መለያየት ሲበልጠው እንደ የመንና ሩዋንዳ ነው። እያየነው ካለነው አርቀን ማየት አለብን። እያሰብን ካለነው ልቀን ማሰብ አለብን። አንድነት በማጣት የፈረሱ፣ ፍቅር ርቋቸው ታሪካቸውን ያበላሹ ልንማርባቸው የሚገባን ብዙ ጎረቤት አገሮች አሉን። ከነሱ መማር አለብን። ጠቢብ ሰው በራሱ ላይ እስኪሆን አይጠብቅም፣ በዙሪያዋ ካለው የሚማር ነው። እኛ ግን ከትላንት እስከዛሬ አንድ አይነቶች ነን። ከሌሎች መማር አልቻልንም። ይሄን ሁሉ ዘመን ተዋግተን፣ ይሄን ሁሉ ዘመን ተገፋፍተን የጦርነትን አስከፊነት አልተረዳነውም**

አይነት ሆነን ኖረናል። አሁን ግን ከፍ እንበል። ያላየነው ሰላም፣ ያልደረስንበት የከፍታ ስፍራ አለና ወደዛ እናዝግም። ለጠላቶቻችን ግብዐት እንዳንሆን የጠላቶቻችንን ሴራ በፍቅር እናክሽፍ። በአንድነት እንስበር። በመካከላችን ከፉዎች የሰሩት ያላለፍነው ትላንትና አለ። በመካከላችን የስልጣን ጥመኞች ያበጁት ያልተሻገርነው ድልድይ አለ። በመካከላችን ከፉ ልቦች ጸንሰውት ነውረኛ እጆች የጻፉት ያልተዳፈነ ታሪክ አለ። በመካከላችን ትላንትን የሚያሳዩን ያልደፈናቸው ሽንቁሮች አሉ። እኚህ በከፉዎች ሆን ተብለው የተበጁ ነውረኛ ታሪኮች የእኔና የእናተን ዛሬና ነገ ከማበላሸት በቀር አላማ የላቸውምና በመጠየቅ፤ ጠይቆም መልስ በማግኘት እንርታቸው።

በአንድነትና በጋራ ትውልድ የሚገልጠውን አዲስ ታሪክ እንጻፍ። እውነት በቃኘው፣ ፍትህ በዋጀው የመነጋገር ባህል አዲስ ነገ እንስራ። አሁን ላለችው ኢትዮጵያ የሚበጃት ይሄ ብቻ ነው። ወደከፍታ ከሚወስዱን በጎ ጎዳናዎች በቀር በሁሉም ላይ ተረማምደናል..ሁሉም ጎዳናዎች ግን አደናቅፈውናል አሁን የሚቀረን ያልሄድንባቸው እነዛ የበጎነት ጎዳናዎች ናቸው። አሁን የሚቀረን ተነጋግሮ መግባባት፣ ተግባብቶ አገር መፍጠር ነው። አሁን የሚቀረን የጠላቶቻችንን ምክር የሚያሳፍር የአንድነት ሀይል ነው። አሁን የሚቀረን ከጦርነት ወደ ሰላም፣ ቤተክርስቲያንና መስኪድ ከማቃጠል ወደ መስራት መሸጋገር ነው። አሁን የሚቀረን በእኛ ከፋት፣ በእኛ አንድነት ማጣት የጠፋችውን ኢትዮጵያ ፈልጎ ማግኘት ነው። አሁን የሚቀረን በእኔነት ውስጥ የጠፋችውን ኢትዮጵያ በእኛነት ውስጥ አስሶ ማግኘት ነው።

እንደ ዜጋ ለአገራችን ያላደረግነው ብዙ ነው..ባለን አቅም፣ ባለን ወጣትነት፣ ባለን ስልጣን ለአገራችን ማድረግ ብንችል ኖሮ አገራችን በዚህ ልክ ስቃይ ላይ ባልወደቀች ነበር። ሩጫችን ሁሉ ወደ እኔነት ስለሆነ አገራችንን ለማሰብ ጊዜ አልነበረንም። ከቀሪው አለምና መንግስት የምንለየው ራስ ወዳድ በመሆናችን ነው..እመኑኝ ሲበዛ ራስ ወዳዶች ነን..ራስ ወዳድ ባንሆን ኖሮ ለሰላምና ለመነጋገር ጊዜ አናጣም ነበር። ለአንድነትና ለወንድማማችነት ቦታ አናጣም ነበር። ሰው እንዴት ራሱን ብቻ ይዞ ይኖራል? ሰው እንዴት ራሱን በቻ እያሰበ፣ ራሱን ብቻ እያፈቀረ ይኖራል? እባካችሁ ሰው እንሁን፤ ራሳችንን ብቻ ሳይሆን ሌላውንም በማፍቀር እንኑር።

እንደዜጋ ከአገራችን ከመጠበቅ በቀር ለአገራችን ምንም አድርገን አናውቅም። ከትላንት እስከዛሬ ራሳችንን ስንጦር፣ ራሳችንን ስናገለግል የኖርን ነን። ስልጣናችንን ተጠቅመን እየሰረቅንና፣ እየዋሸን፣ እየዘረፍንና የማይሆን ነገር እያደረግን የመጣን ነን። አገር ሰው ትሻለች፤ የራሱ ብቻ ያልሆነ ሰው። መቶ ሀያ ሚሊዮን ህዝብ ያላት አገር ሰው ስታጣ፣ አስታራቂ ስታጣ፣ የሰላም ሰው ስታጣ፣ ሽማግሌ ስታጣ፣ ይቅር ባይ ስታጣ፣ የተማረ ስታጣ፤ እልፍ ልጅ የወለደች አገር ተቆርቋሪ ስታጣ፣ ተነጋግሮ የሚግባባ ትውልድ ስታጣ፣ ስለሌላው ግድ የሚለው ሰውነት ስታጣ እንደምን አይገርምም?። ከዚህ በላይ አለም የሚያስገርም ነገር የላትም። ጥሩ ታሪክ ሰርተን መጥፎ ታሪካችንን እንቀይር ዘንድ ጊዜው አሁን ነው። እስከዛሬ የዘጋናቸውን መንገዶች ለሌሎች እንክፈት። እስከዛሬ የዘጋናቸውን ልቦቻችንን ለትህትና እንክፈት። ተነጋግሮ መግባባት ለዚች የኋላቀርነት ፈንገል ለሚያንደፋድፋት አገራችን፣ የኋላቀርነት ቆላ ቁስል ለሚያሰቃየው ህዝባችን ፍቱን መድሀኒት ነውና የእይታ መነጽራችንን አስተካክለን ከትላንት የላቀ፣ ከዛሬ የደመቀ ነገን አሻቅበን እናይ ዘንድ ያስፈልገናል።

አለመግባባት ከጎዳን ተግባብቶ መጠቀም ለምን አቃተን? ብሄርተኝነት ካልበጀን ኢትዮጵያዊነትን መሀከል አድርጎ መኖር ለምን ከበደን? እኔነት ድልድይ ሆኖ ወንዝ ካላሻገረን እኛነትን መምረጥ ለምን ተሳነን? መጠየቅ ብንችል መልሶቻችን ቀላሎች ነበሩ። ችግሩ ግን መጠየቅ አንወድም። ብንጠይቅ ላለማመን ስለቆምን ለማመን የሚሆን አቅም የለንም። በብዙ ነገር የባከንን ህዝቦች ነን፣ በብዙ ነገር ከስልጣኔና ከዘመናዊነት የሸሸን ህዝቦች ነን። በገዛ እጃችን መድረስ ካለብን ያልደረስን ነን። በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ለሰላም የሚሆኑ አማራጮችን ማየት እንጂ የትላንትን ስህተት መድገም አይኖርብንም። የቀረንን ሙጣጭ አቅም ኢትዮጵያን ለመስራት እንጠቀምበት። በአገራዊ ምክክር ሂደት ውስጥ ሀሳብ እናዋጣበት። አንድነትን እንገንባበት። ታሪክ ወለድ የሆኑ የእብለት ትርክቶችን እናጋልጥበት። በእናታቸው ማህጸን ውስጥ ብኩርናን ሽተው ለአንደኝነት እንደተጋፉት እንደ ርብቃ ልጆች በእኛ ግፊያ ያዘመመች ቤታችንን እንታደግበት። ከረፍታችን ለመድረስ ለራሳችን ውለታ እንዋል።

ፖለቲካችንን ብንመረምረው በርካታ ያልተጠየቁ፣ በርካታ መልስ ያላገኙ፣ በርካታ ህዝብ የማያውቃቸው ታሪኮችን እናገኛለን። ትላንትን ብንፈትሸው ህዝብ የማያውቀው፣ ትውልድ ያልደረሰበት በወንድማማቾች መካከል መቃቃርን እንዲፈጥሩ ሆነው የተቀመጡ የፖለቲካ ሴራዎችን እናገኛለን። ግን አንጠይቅም፤ ግን ለምን አንልም። ለፖለቲካ ወለድ ችግሮቻችንንም ሆኑ ለሌሎች ችግሮቻችን በመጠየቅ ውስጥ አስተማማኝ መልስን የማግኘት ባህልን ማዳበር ይኖርብናል። እኔ ግን እጠይቃለው፤ ስለ አገሬ፣ ስለህዝቤ ምንድነው ያጣነው? ስል ሁሌ ራሴን እጠይቃለው። ምንድነው የሌለን? ስል ነጋ ጠባ ራሴን አስጨንቃለው። እስከዛሬ ጠይቄ፣ እስከዛሬ ተመራምሬ እንደ አገር ያጣነውን ግን ልደርስበት አልቻልኩም። እውነት ያጣነው ምንም የለም። ከፍቅር ሌላ፣ ከትህትና ሌላ፣ ከይቅርታ ሌላ፣ ከመተው ሌላ ያጣነው ምንም የለም። በአንድነትና በወንድማማችነት መንፈስ ተቃቅፎ የጋራ ቤት ለመስራት ከመትጋት ባለፈ ያጣነው ምንም የለም። ብዙ አገራት ምንም ሳይኖራቸው በፍቅር ብቻ ተዐምር ሰርተዋል። እኛ ብዙ እያለን ፍቅር በማጣት ብቻ ተዐምራችንን ሰውረናል። ይሄ የምንግዜም አግራሞቴ ሆኖ ልቤ ውስጥ አለ።

አገር ፍቅር ሲርቃት፣ አንድነት ስታጣ ሶርያን ናት። ህዝብ ጥላቻና መለያየት ሲበልጠው እንደ የመንና ሩዋንዳ ነው። እያየነው ካለነው አርቀን ማየት አለብን። እያሰብን ካለነው ልቀን ማሰብ አለብን። አንድነት በማጣት የፈረሱ፣ ፍቅር ርቋቸው ታሪካቸውን ያበላሹ ልንማርባቸው የሚገባን ብዙ ጎረቤት አገሮች አሉን። ከነሱ መማር አለብን። ጠቢብ ሰው በራሱ ላይ እስኪሆን አይጠብቅም፣ በዙሪያዋ ካለው የሚማር ነው። እኛ ግን ከትላንት እስከዛሬ አንድ አይነቶች ነን። ከሌሎች መማር አልቻልንም። ይሄን ሁሉ ዘመን ተዋግተን፣ ይሄን ሁሉ ዘመን ተገፋፍተን የጦርነትን አስከፊነት አልተረዳነውም። በእኛ ካልደረሰ መከራና ችግር እንዳይገባን ሆነን የቆምን ህዝቦች ነን። ፖለቲካችን ከትላንት እስከዛሬ አንድ አይነት ነው። አስተሳሰባችን ዛሬም እንደጥንቱ ነው። ዛሬም ድረስ ከጥፋት ያልዳነው፣ ዛሬም ድረስ ከብሄር ፖለቲካ ያልተለየነው እኮ ከትላንት አስተሳሰብ ስላልወጣን ነው። በልባችን ብዙ ሀሳብ ሊኖር ይችላል፣ ለአገራችን ልንሰራ፣ ለህዝባችን ዘብ ልንቆም የቆረጥን እንኖር ይሆናል ይሄ ሁሉ ብርሀናዊ ተስፋችን እውን የሚሆነው ከትላንት አስተሳሰብ መላቀቅ ስንችል ብቻ ነው።

ከትላንት የሸሸ፣ በበጎነት የገነነ፣ ስለአገሩ ግድ የሚሰጠው ዜጋ ያስፈልገናል። አገሬ ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትረሳኝ፣ ብክድሽ፣ ባዋርድሽ የቆምኩባት ምድር ትፍረደኝ የሚል ትውልድ እንሻለን። አገሩን ከፊት አስቀድሞ የሚከተል እግር፣ ወገኑን ከፊት አድርጎ የሚያስብ አእምሮ ለአዲሷ ኢትዮጵያ ዋልታና ማገር ነው እላለው። ስንት ጊዜ እንፍረስ? ስንት ጊዜ እንድማ? በታደሰ ልብ ወደ ፊት እንጂ ከእንግዲህ የትላንት የፖለቲካ ማህጸን የጸነሰውን የዘረኝነት ሽል ታቅፈን እዬዬ የማይታሰብ ነው። ጫንቃችን ላይ በተጫነ የእኔነትና የጎጠኝነት ደዌ መታመም ይበቃናል።

በፖለቲካ ትርፍና በእልኸኝነት የጎበጠ ጀርባችንን ሳናቀና ሌላ የነገር ቁርሾ ይዘን በቆረቆር ላይ ቁምጥና መሆን የለብንም። እኛን ሳስብ ብዙ ነገር ይገርመኛል፤ ከአግራሞቴ አንዱ በአንድ ወንዝ እየፈሰስን፣ ከአንድ ወንዝ እየተቀዳን፣ በኢትዮጵያዊነት ክርና መርፌ ተሰፍተንና ተደውረን፣ ተደባልቀንና ተቀይጠን ስናበቃ በዚህ ቁርኝት ውስጥ ሌላነትን ለመፈለግ መንፈራገጣችን ነው። ሰው እንዴት ከራሱ ጋር ይጣላል? ሰው እንዴት ከራሱ ጋር ሆድና ጀርባ ይሆናል? በኢትዮጵያ ምድር ሌላ ሰው የለም። ሌላ ብሄር፣ ሌላ ሀይማኖት የለም። ሁላችንም ኢትዮጵያን የፈጠርን፣ ኢትዮጵያን የሰራን አንድ አይነት ነፍሶች ነን። ታሪካችን፣ ባህላችን፣ ልማዳችን ተደባልቆ አንድ አይነት እኛን ፈጥሯል። አጠገባችን ያለን ሰው ስንገፋ፣ ስንጠላ፣ ራሳችንን እየገፋንና እየጠላን እንደሆነ ልናውቅ ይገባል። አገሬ ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ ይህ የዚህ ዘመን ብሄራዊ መዝሙር እንዲሆን እሻለው።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# በመኸሩ ሁለገብ የግብርና ሥራ በጅማ ዞን

**ስምስም መንግሥቱ**

ገበሬው በአጭር ታጥቆ ለግብርና ሥራ እራሱን ዝግጁ የሚያደርግበት ወቅት ላይ ነው የምንገኘው። ለነገሩ ገበሬው አመቱን ሙሉ ከግብርና ወደ ግብርና ሥራ ከተሸጋገረ ሰነባብቷል። ይህን ባህል በማዳበር ብዙ ሥራ የሚቀር ቢሆንም፤ ገበሬው የመኸር ወቅትን ብቻ ጠብቆ የግብርና ሥራ ያከናውንባቸው የነበሩ ጊዜያቶች ማለፋቸው እየተነገረ ብቻ ሳይሆን፣ በተግባርም እያየን ነው። ከመኸሩ የግብርና ሥራ ጀምሮ በበጋ የቆላ መስኖና በበልግ የሰብል ግብርና ሥራና በጓሮ አትክልት ልማት ጭምር በግብርና ሥራው ላይ ነው የቆየው። አሁን ደግሞ ዋናው የግብርና ሥራ በሚከናወንበት የክረምት ወቅት ላይ በመሆኑ የመኸሩ ዝግጅት የበለጠ ነው የሚሆነው። የገበሬው ባጭር ታጥቆ ሞፈርና ቀንበሩን ማዘጋጀት ወይንም በዘመናዊው የእርሻ መሣሪያ ዘዴ ትራክተር ለመጠቀም መሰናዳት ብቻውን በቂ አይደለም። ለእርሻ ሥራው የሚያስፈልጉ ግብአቶችም አብረው መሟላት ይኖርባቸዋል። በተለይም በዚህኛው የመኸር የግብርና ወቅት በዓለም ላይ ዋጋው እየናረና በአገር ውስጥም ባጋጠመው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያቶች የማዳበሪያ አቅርቦት ቀደም ባሉት አመታት እንደነበረው እንደማይሆን ይጠበቃል። አርሶአደሩ እየተበረታታ ያለው የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲጠቀም ነው። በዚህ ረገድ ሁሉም በየአካባቢው ዝግጅት ማድረግ እንደሚጠበቅበትም መረጃዎች ቀድመው መሰራጨታቸው ይታወሳል። እኛም ለዛሬ የተፈጥሮ ማዳበሪያን በማዘጋጀትና በአጠቃላይ በመኸር የግብርና ሥራ ዙሪያ የጅማ ዞንን እንቅስቃሴ ከዞኑ ቡና ልማት፣ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ኤልያስ እንድሪያስ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን፤ በ2014-2015 ዓ.ም የምርት ዘመን ላይ የምንገኝ ቢሆንም ያለፈው የምርት ዘመን ለዚህኛው ተሞክሮ የሚገኝበት በመሆኑ የነበረውን ሂደት ያስታውሱንና በወቅታዊው ላይ ትኩረት እናድርግ።**

**አቶ ኤልያስ፤** በቆላ የበጋ መስኖ የለማው ሰብል ተሰብስቦ ወደ ቀጣዩ የግብርና ሥራ ሽግግር የምናደርግበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ዝግጅትም እየተደረገ ነው። በቆላ የበጋ መስኖ ልማት የተለያየ የሰብል ልማት የተከናወነ ሲሆን፣ በአብዛኛውም የተከናወነው ግን የስንዴ ልማት ነው። ምርቱም ከማሳ ላይ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል። በዞኑ የበልግ እርሻ ተብሎ የሚያዝ ዕቅድ የለም። የተለመደም አይደለም። ይሁን እንጂ በዞኑ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ሰፋ ያለ መሬት የሚሸፈን ሲሆን፣ ወደ 550ሺ ሄክታር መሬት ይገመታል። በአካባቢው በተለመደው የእርሻ ሥራ ዋናው የመኸር የግብርና ሥራ ከሚከናወንበት የክረምት ወቅት ቀድሞ ነው ሥራ የሚጀመረው። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ የመኸሩ የግብርና ሥራ ተጀምሯል። የአገዳ ሰብል ልማት ሥራ በማሳ ላይ ሰፊ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ቀድሞ ነው የሚጀመረው በአሁኑ ጊዜም ዘር መዝራት የጀመሩና ዝግጅት ላይ የሚገኙ አሉ። በተያዘው የመኸር የግብርና ሥራ ወደ 552ሺ ሄክታር መሬት በተለያየ ሰብል በመሸፈን ለማምረት ነው የታቀደው። ባለፈው የምርት ዘመን 550ሺ ሄክታር መሬት ነው በተለያየ ዘር በመሸፈን የግብርና ሥራው ተከናውኗል። በዘንድሮው መኸር እስካሁን ባለው ክንውን ወደ 70 በመቶ የሚሆን ሥራ ተሰርቷል። በ2014-2015 ምርት ዘመን ከ19ሚሊየን ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል።

ዕቅዱን ለማሳካት፣ ግብአቶችን ቀድሞ ማቅረብ፣ አርሶአደሩም የሚፈልገውን እገዛ እንዲያገኝ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን መስጠት የሚጠበቁ ተግባራት በመሆናቸው በጽህፈት ቤቱ በኩል አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተሰርተዋል። ከግብአት አቅርቦት ጋር በተያያዘ የማዳበሪያ አቅርቦት ችግር ዓለምአቀፍና አገርአቀፍ በመሆኑ ይህን ታሳቢ ያደረገ መፍትሄ በመፈለግ ምርትና ምርታማነቱን የማሳደግ ሥራ ተጠናክሯል። ከሚደረጉት ጥረቶች አንዱ የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) ጥቅም ላይ እንዲውል ሲሆን፣ አርሶ አደሩ ቀድሞ ዝግጅት እንዲያደርግ የንቅናቄ ሥራ ተሰርቷል።

የግብርና ሥራ በአንድ የሰብል ልማት ላይ ብቻ ማተኮር የለበትም። ሁለገብ ነው መሆን ያለበት በመሆኑም በጅማ ዞን ሁለገብ የግብርና ሥራ ነው በመከናወን ላይ የሚገኘው።ከሰብል ልማቱ ጎን ለጎን የቡና፣ የአትክልት፣ የእንስሳት ልማቶች ይከናወናሉ። በጅማ ዞን ከሰብል ልማት ቀጥሎ በዋና ልማት የሚያዘው የቡና ልማት ነው። 80 በመቶ የሚሆነው የአካባቢው ማህበረሰብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከቡና ጋር የተቆራኘ ነው። የኑሮ መሰረቱ ነው ማለት ይቻላል። ልክ ለመኸር የሰብል ልማት የሚደረግ ዝግጅት ለቡና ልማትም በተመሳሳይ ዝግጅት ይደረጋል። ለቡና ችግኝ መትከያ የሚሆን ጉድጓድ ይቆፈራል። በዚህ ወቅት ማንኛውም የግብርና ሥራ በኩታገጠም (ክላስተር) ስለሚከናወን ቡናን ጨምሮ በክላስተር ነው የግብርና ሥራው የሚከናወነው። በዚህ መሠረት ወደ490ሺ በሚሆን ማሳ ላይ የቡና ልማት በማካሄድ ምርታማነቱን የመጨመር ሥራ ይሰራል። አትክልትና ፍራፍሬ ልማቱም ጎን ለጎን የሚከናወን በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥላል። በአሁኑ ጊዜም የአቮካዶና የሙዝ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለአርሶአደሩ በማከፋፈል ልማቱን የማሳደግ ሥራ እየተሰራ ነው። ልማቱ የወጭ ንግድንም ታሳቢ ያደረገ በመሆኑ በትኩረት ነው የሚከናወነው። አምና ወደ 40 ኩንታል የአቮካዶ ምርት ለአውሮፓ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ተችሏል።በዘንድሮ የምርት ዘመን በስፋት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል። ንብ ማነብ ከእንስሳት ልማት አንዱ ነው። አካባቢው ለንብ ማነብ ምቹና የሀብቱ መገኛ ነው።በዚህ ረገድም የማር ልማቱን ለማዘመን ብዛት ያለው የንብ ቀፎ ለአልሚው በማሰራጨት ሰፊ ሥራ እየተሠራ ሲሆን፣ እስካሁንም ከ28ሺ በላይ ዘመናዊ የንብ ቀፎ ተሰራጭቷል።በነበረው ተሞክሮ የንብ ቀፎ ስርጭቱ ከ20 በታች ነበር። የንብ ቀፎ ስርጭት ቁጥሩ ከፍ እያለ መምጣት የልማቱ እድገት አንዱ ማሳያና ለዘርፉም እየተሰጠ ያለውን ትኩረት ያመላክታል። ይሄ ትልቅ ስኬት ነው።

**አዲስ ዘመን፤ በ2014-2015 የምርት ዘመን ከ19 ሚሊየን ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ሲታቀድ መነሻው ምንድ ነው?**

**አቶ ኤልያስ፤** ያለፈውን የምርት ዘመን ነው መነሻ ያደረግነው። በ2014-2015 የምርት ዘመን 18 ነጥብ 7 ሚሊየን የሚጠጋ ምርት ነው የሰበሰብነው። ከ2013-2014 የምርት ዘመን ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው። ይህ በአጠቃላይ በዞኑ ምርታማነት እያደገ መምጣቱን ያሳያል።ለእድገቱ መመዝገብ ደግሞ በየምርት ዘመኑ የሚሰሩ ሥራዎች ለውጥ እያመጡ መሆናቸውን ነው። ለውጡ የግብርና ግብአትን ቀድሞና በመጠንና አስፈላጊውን አሟልቶ በማቅረብ እንዲሁም በክትትልና ድጋፍ የተሻለ እንቅስቃሴ በማድረግ ይገለጻል። አርሶአደሩ ለዘመናዊ የአመራረት ዘዴ የሰጠው ትኩረትና በመተግበረም ያሳየው ተነሳሽነት ለእድገቱ ተጨማሪ አቅም ፈጥሯል። በተለይም በዘመናዊው የአመራረት ዘዴ አርሶአደሩ በትራክክተር በማረስና ምርት መሰብሰብ ደረጃ መድረሱ ትልቅ ለውጥ ነው። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ባለፈው አመት የምርት ዘመን ብቻ በአማካይ 10ነጥብ3 በመቶ ምርታማነትን መጨመር ተችሏል።ይሄ በኩንታል ወደ አንድ አራት ነጥብ አራት ሚሊየን ሲሆን፣ በአንድ አመት የተመዘገበ ውጤት ነው። የተጀመሩት ሥራዎች ከተጠናከሩና አዳዲስ አሰራሮችንም መጨመር ከተቻለ የበለጠ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻልና ትልቅ አቅምም መኖሩን ያሳያል። አሁንም መሥራቱ ላይ ማተኮር እንደሚገባ ግንዛቤ ተይዟል። ዘንድሮም ከአንድ ሚሊየን ኩንታል በላይ ለመጨመር ነው የታቀደው።

**አዲስ ዘመን፤ የዘንድሮው ከባለፈው የምርትዘመን ከፍ ብሎ ሲታቀድ ለግብርና ሥራው የተመቻቹ ሁኔታዎች ተፈጥረው ነው?**

**አቶ ኤልያስ፤** ተግዳሮች እንደሚኖሩ ታሳቢ ተደርጓል። አርሶአደሩ የሚፈልጋቸው የምርጥ ዘር ዝርያ አቅርቦት ከሌለ የሚፈለገው ውጤት ላይገኝ ይችላል። ለአብነትም የበቆሎ ምርጥዘር ዝርያ ይጠቀሳል። ሊሙ፣ ሾኔ፣ ፓዮኔር የበቆሎ ዝርያዎች ይፈለጋሉ። በምርት ዘመኑ በተለያየ ዘር ለመሸፈን በዕቅድ ከተያዘው ከ552ሺ ሄክታር መሬት ውስጥ ወደ 180ሺ ሄክታር የሚሆነው በበቆሎ ዘር ነው የሚሸፈነው። አርሶአደሩ የሚፈልገው የምርጥ ዘር አይነት መቅረቡ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ወሳኝ ነው። ነገር ግን የመሟላቱ ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ ስለሆነ በሌላ ዝርያ በመተካት ልማቱን ማከናወን ደግሞ ግድ ነው። ክፍተቶች ቢኖሩም የአካባቢውን ስነምህዳር መሰረት ያደረገ የሥራ አቅጣጫ በማስቀመጥ ከሚከናወነው በተጨማሪ መገናኛብዙሃንን በመጠቀም ከአርሶአደሩ ጋር ለአንድ ሰአት ያህል የቀጥታ ውይይት ይካሄዳል።ውይይቱ በተለያየ ርስጉዳይ ሲሆን፣አሁን ያለው ወቅታዊ ሁኔታ የምርጥዘርና የተፈጥሮ ማዳበሪያ ዝግጅት በመሆኑ በትኩረት ምክክር ይደረግበታል።በዚህ ውይይትም አርሶአደሩ የተለያዩ ጥያቄዎች ቢኖሩት የመጠየቅና መልስ የማግኘት መብት አለው። እንዲህ ያለው የውይይት መድረክ መመቻቸቱ አርሶአደሩ ቀጥታ ከባለሙያ ጋር ካለው ግንኙነት በተጨማሪ በባለሙያው ያልተመለሱለት ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ዕድል ያገኛል።



ፎቶ፡- ስምስም መንግሥቱ

**አዲስ ዘመን፤ አርሶአደሩ የሚፈልጋቸው የበቆሎ ዘር አይነት አቅርቦት አለመኖር መነሻ ምክንያቱ ምንድነው?**

**አቶ ኤልያስ፤** ምንጩን ወይንም የተፈጠረውን ክፍተት በሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን።አንዱ በእኛ በኩል የሚፈታ ነው። ሌላው በሌላ አካል የሚፈታ ነው። ለአብነትም በአርሶአደሩ በኩል በጣም ተፈላጊ የሆኑት የፓዮኔር ዝርያ በዞኑ አቅም የሚፈቱ አይደሉም።በክልሉ አስተዳደር ወይንም በፌዴራል ደረጃ የሚፈቱ ናቸው። ጥያቄው በተለያዩ መድረኮች ቀርቧል። ከሚመለከታቸው የዘርፉ የበላይ አመራሮች ጋርም ውይይት ተካሂዷል። እስካሁን ያለማቋረጥ ጥያቄው እየቀረበና እየተነጋገርንበት ቢሆንም ችግሩ እየጨመረ እንጂ መፍትሄ እያገኘ አይደለም። መፍትሄ ለማስቀመጥ ጥረቶች ቢኖሩም ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይጠይቃል። አርሶአደሩ ዝርያውን በደንብ የሚያውቀው በመሆኑ በቀላሉ እንዲተወው ማድረግ ያዳግታል። እኛ ሳይንስን መሰረት በማድረግ ሌላ የዝርያ አይነት እንዲጠቀም ነው የምንነግረው እርሱ ደግሞ የትኛው ዝርያ ከየትኛው እንደሚሻል በተግባር ነው የሚያየው።ዝርያውን አባዝተው የሚያቀርቡት ኩባንያዎች ናቸው። ዘላቂ መፍትሄ ይሆናል ብዬ የማስበው መንግሥት ጣልቃ ገብቶ ኩባንያዎቹ ዘርፉን አባዝተው የሚያሰራጩበትን መንገድ እንዲያመቻች ነው።

**አዲስ ዘመን፤ በዝርያ አቅርቦቱ ላይ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር ውይይት በሚኖራችሁ ወቅት የምታገኙት ምላሽ ምንድነው?**

**አቶ ኤልያስ፤** ሁለት ምላሽ ነው የምናገኘው። አንዱ በአካባቢ ላይ በሚገኝ ዝርያ አይነት መጠቀም ወይንም እንዲተካ ማድረግ ነው። ሌላው በረጅም ጊዜ ደግሞ የዝርያ ብዜቱን በመጨመር ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት የሚል ነው። እንደ ሙያ ሲወሰድ በአካባቢ የዝርያ አይነት መተካት የሚለው ትክክል ነው። በተመሳሳይ ሥነምህዳር ውስጥ ሊሆኑ የሚችሉ ዝርያዎች አሉ። ያንን እየተኩ መሄድ ይቻላል። እዚህ ላይ ያለው ተግዳት አርሶአደሩ የትኛው ከየትኛው ዝርያ በምርታማነት እንደሚበልጥ በተግባር የሚያውቀው በመሆኑ ማሳመኑ ላይ ነው። ለጊዜው ሊጠቀም ይችላል። የሚተገበረው ግን በፍላጎት ደስተኛ ሆኖ አይደለም። ጉዳዩ ከአገር አቅም በላይ መሆኑም ይታወቃል። የእናት ዝርያ የሚባለው ከውጭ እንደሚገባና በአገር ውስጥ ተባዝቶ የሚቀርብ መሆኑ ይታወቃል። ፓዮንየር የተባለው የበቆሎ ዝርያ ተባዝቶ ይቀርብ የነበረው በምዕራቡ የኢትዮጵያ ክፍል ቤንሻንጉልና ጋምቤላ ክልሎች ነው። በነዚህ አካባቢዎች የተከሰተው የፀጥታ ችግር ዘር በማባዛቱና በስርጭቱ ላይ ተጽዕኖ ፈጥሯል። እንደአገርም በጦርነት ውስጥ መቆየታችንና የኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ መከሰትና በነዚህ ተጽዕኖዎች የውጭ ምንዛሪ እጥረት ማጋጠም የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ተደማምሮ ችግሩን የከፋ አድርጎታል።

**አዲስ ዘመን፣ በግዥ ከውጭ ይገባ የነበረውን ማዳበሪያ በአገር ውስጥ ለመተካት የሚደረገው የተፈጥሮ ማዳበሪያን የማዘጋጀት እንቅስቃሴ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ኤልያስ፤** የተፈጥሮ ማዳበሪያ አዘጋጅቶ መጠቀም በኢትዮጵያ የመጀመሪያ አይደለም።በመሆኑም ልምዱ አለ። አሁን ደግሞ በዓለም አቀፍ የማዳበሪያ ዋጋ መጨመሩ በመንግሥት ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ተሞክሮ የማሳደግ ሥራ ነው የሚሰራው። በኦሮሚያ ክልል አስተዳደር የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲዘጋጅ ቀደም ብሎ አቅጣጫ በመቀመጡ ዝግጅቱ ቀድሞ ነው የተጀመረው። ኮምፖስት ለማዘጋጀት ጊዜ ስለሚወስድ ቀድሞ ነው ዝግጅት መደረግ ያለበት። በአሁኑ ጊዜም በዞኑ በተለያየ መንገድ እየተዘጋጀ ነው። አንዱ መሬት ውስጥ ተቀብሮ እስከ 20 እና 25 ቀናት እያገላበጡ የሚከናወነው ነው። ሌላው በትል የሚከናወነው በርሚ ኮምፖስት የሚባለው ነው። ተመራጭ ኮምፖስት ነው። የትሉ ዝርያ ከእስራኤልና ከህንድ ነው የሚመጣው። በዞኑ ውስጥ ወደ 135 ሺ አርሶአደሮች እየሰሩ ይገኛሉ። ወደ 120ሺ ኩንታል የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከትል ተዘጋጅቷል። በዞኑ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማዘጋጃዎች በመገንባት ላይ ናቸው። አንዱ ግንባታ በዞኑ ጌራ ወረዳ ላይ ሲሆን፣በወር እስከ 180 ኩንታል በርሚ ኮምፖስት የሚያዘጋጅ ነው። ማእከሎቹ ኮምፖስት ማዘጋጃ ብቻ ሳይሆኑ አርሶአደሩም ክህሎት የሚያገኙባቸው ናቸው። የትላትል ዘርም በማዕከሎቹ እንዲገኝ ይሰራል። ባዮሲለር የሚባል የኮምፖስት አዘገጃጀት ዘዴም እየተከናወነ ነው።ባዮጋዝ ኃይል አመንጭቶ ከውስጡ የሚወጣው ተረፈምርት ለማዳበሪያ ጥቅም ይውላል።ወደ አራት ነጥብ አራት ሚሊየን ሜትር ኪዩብ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማምረት ነው ታቅዶ እየተሰራ ያለው። እስካሁን በግማሽ ተከናውኗል።

**አዲስ ዘመን ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ**

**አቶ ኤልያስ፤** እኔም አመሰግናለሁ

ማህበራዊ

# አስኳላ

# “መጻሕፍትን ለተቋማት መለገስ እውቀትን ለትውልድ እንደማስረከብ ይቆጠራል”

\- አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ

ግርማ መንግሥቴ

ባለፈው ሳምንት በዚሁ አምድና ገጽ ላይ “ወሰኑ እስከ መጻሕፍት ልገሳ የዘለቀው ኢትዮጵያዊ እሴት” በሚል ርእስ ከዛሬው ርእሳችን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ጽሑፍ ለንባብ አብቅተን ነበር። ፕሬስ ድርጅትም “በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆነውና ጫማ በመጥረግ የሚተዳደረው ወጣት ታሪኩ ወዬሳ 975 መጻሕፍት ለአብርሆት ቤተ መጻሕፍት እንዲደርስለት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አበርክቷል።” “የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለአብርሆት ቤተ-መጽሐፍት ያሰባሰበውን ከአምስት ሺህ በላይ መጻሕፍት አስረከበ።” (“በአምስት ቀን አምስት ሺህ መጽሀፍ” በሚል ሃሳብ ባካሄደው የመጽሃፍ ማሰባሰብ መርሃ-ግብር ከእቅዱ በላይ መጻሕፍት ማሰባሰብ መቻሉን የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በርክክቡ ወቅት መናገራቸውም ይታወሳል።) የሚሉ ዜናዎችን ማስነበቡም ይታወሳል። ዛሬም በዛ ጽሑፍ ያነሳናቸውን ፍሬ ሀሳቦች በተግባር ያረጋገጡ ሊጋስን እንግዳችን አድርገናል።

እንግዳችን አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ ይባላሉ። ነዋሪነታቸው እዚሁ አዲስ አበባ፣ ፈረንሳይ አካባቢ ሲሆን፤ የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ድርጅት ባልደረባ ናቸው።

አቶ አስፋወሰን የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያገኙ ሲሆን፤ ከመጻሕፍት ጋርም የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። በተለይም ከአንባቢና ተመራማሪ ቤተሰብ መውጣታቸው ለዛሬው ሰብእናቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳደረገም ነው በቀጥታም ባይሆን በገደምዳሜው የነገሩን። (አባታቸው አቶ ሺመላሽ በቀለ ሲበዛ አንባቢ፣ የሶስት መጻሕፍት ደራሲ፣ በንጉሱ ዘመን በተለያዩ የመንግስት ተቋማት በኃላፊነት የሰሩ ከመሆናቸውም በላይ ለ11 አመታት በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር ዜን ሴክሬታሪ በመሆን ያገለገሉ ሰው መሆናቸውን አቶ አስፋወሰን አጫውተውናል።)

ለዚህ አምድ የዛሬ እንግዳችን ልናደርጋቸው በማሰብ ስንጠይቃቸው ላሳዩት ትህትናና ፈጣን ትብብር እያመሰገንናቸው ወደ አደረግነው ቃለ ምልልስ እንሂድ።

**አዲስ ዘመን፡- የተለያዩ መጻሕፍትን ለግሰዋል የሚባል ጭምጭምታ ሰምተናል፤ እውነት ነው?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** አዎ፤ እውነት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙን ሲነግሩን ይችላሉ?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** አዎ፣ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው የሰጠሁት።

**አዲስ ዘመን፡- ምን ያህል መጻሕፍትን ለገሱ?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** 120 መጻሕፍት ነው የሰጠሁት።

**አዲስ ዘመን፡- ለማወቅ ባደረግነው ጥረት የሰጧቸው መጻሕፍት ለየት ያሉ ናቸው የሚል ነገር ሰምተናል። መጻሕፍቱን ምንድን ነው ለየት የሚያደርጋቸው?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** መጻሕፍቱ በሙሉ ማለት በሚቻል ደረጃ የሕግ፣ ሕገ መንግስትና የፍልስፍና መጻሕፍት ናቸው። በይዘት ደረጃ ላቅ ያሉ ናቸው። አንዳንዶቹን ዩኒቨርሲቲው የሌለው ናቸው። ገበያም ላይ በቀላሉ የሚገኙ አይደሉም። በተለይ አገር ውስጥ የሚታሰብ አይደለም። ተከታታይ ቅፆችም መሆናቸው ሌላኛው ልዩነታቸው ነው። በዋናነት እነዚህ ናቸው ልዩ የሚያደርጓቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ስመሆኑ ለዚህ አይነቱ የተባረከ ሀሳብ ያነሳሳዎት ምክንያት ምንድን ነው፤ በተለይ በዚህ መጻሕፍት ውድ በሆኑበትና ብዙ ገንዘብ ሊያስገኙ በሚችሉበት ሰአት በዚህ ደረጃ ያሉ መጻሕፍትን እንዲለግሱ የገፋፋዎትን ምክንያት ቢነግሩን?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** ይህን እንዳደርግ የገፋፋኝ ወይም ያሳሰበኝ ጉዳዩ የትውልድ ጉዳይ፣ የአገር ጉዳይ በመሆኑ ነው። አንባቢ ትውልድ መፈጠር አለበት። በእውቀት የታነፀ ትውልድ መፈጠር አለበት። ለዚህ ደግሞ እውቀት ያስፈልጋል። ተገቢውን እውቀት ለመቅሰም ደግሞ መጻሕፍት ያስፈልጋሉ። በመሆኑም መጻሕፍቱን በተደራጀ መልክ አዘጋጅቶ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን አመንኩበት። አደረኩትም። ባጭሩ ይኸው ነው።


ADDIS ABABA UNIVERSITY

INSTITUTE OF ETHIOPIAN STUDIES

Addis Ababa Ethiopia

☎(251-1) 23 97 40 E-mail: ies@aau.edu.et

Website: www.aau.edu.et/ies

Date: April 1,2022

Ref.No. ኢጥምተ/73/22/14

**To Asfawossen Shimelash Bekele**

**Subject: Acknowledgement**

This is to acknowledge the receipt of 120 books on **American Jurisprudence** with different titles. These materials will be readily made accessible to researchers and it will be preserved for posterity. As you have made valuable additions to our library collection, please accept our sincere thanks and appreciation. We sincerely appreciate any further donation you may make in the future to build a strong Ethiopian Studies Library.


With regards

Eyob Alemayehu

Institute of Ethiopian Studies Library Deputy Head

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰጣቸው ደብዳቤ





ከለገሷቸው መፃህፍት በከፊል

**አዲስ ዘመን፡- ከንባብ ባህል አኳያ አሁን ያለውን ሁኔታ እንዴት ያዩታል፣ አንባቢ ጠፍቷል የሚሉ አሉ፤ እርስዎ በዚህ ይስማማሉ?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** አይ፣ እኔ ሙሉ ለሙሉ “የለም” ወይም “ጠፍቷል” የሚል ማጠቃለያ የለኝም። ከቀድሞው ትውልድ አኳያ ሲታይ እውነት ነው ደክሟል፤ ደከም ያለ ነገር አለው። እንዲሁ “አንባቢ የለም” የሚለው ግን አያስኬድም፤ የሚያነቡ አሉ። የቀድሞውን ትውልድ በተመለከተ እሱ ከባድ ነው፤ ያ ትውልድ ከባድ ነው። ለዛውም ምንም አይነት የቴክኖሎጂ እገዛ በሌለበትና ነገሮች እንዳሆኑ ባልቀለሉበት በዛ ዘመን ከመጻሕፍት (ሀርድ ኮፒ) ጋር ታግሎ ነው በዛ ደረጃ አንባቢ የነበረው። የቀድሞው ከባድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መጻሕፍቱን በመለገስዎ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኩል ያገኙት ምላሽ ምን እንደሚመስል ቢያጫውቱን?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጣም ነው የተደሰተው። ኃላፊዎቹ እጅግ ተደስተዋል። በተለይም የመጻሕፍቱን ይዘቶች ሲመለከቱ ከመገረምም አልፈው በጣም ደስተኞች ነበሩ። ተደስተዋል።

**አዲስ ዘመን፡- መደሰት ብቻ ነው፤ ወይስ ሌላ ...**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** ብዙ ነገር ነው ያደረጉልኝ። የምስክር ወረቀትና ደብዳቤ ሰጥተውኛል። የዩኒቨርሲቲው ቤተ መጻሕፍት አባል አድርገውኛል። በምፈልግበት ግዜ ሁሉ ገብቼ እንድጠቀም የሚያስችል እድልን ሁሉ ሰጥተውኛል።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ደስተኛ ነዎት?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** አዎ፣ እኔ ለመስጠት ስወስን እነዚህን ነገሮች አስቤ አይደለም። መስጠት እንዳለብኝ ወሰንኩ፤ ሰጠሁ። ይሄው ነው። በእርግጥ እንደዚህ አይነት ምስጋናና ልዩ እድልን በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ። ዩኒቨርሲቲውን አመሰግናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ከሌሎቹ ተቋማት በተለየ እንዴት መረጡት?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** ምክንያቴ ዩኒቨርሲቲ ማለት የሁሉም ስለሆነና መጪው ትውልድ በዚሁ ተቋም ውስጥ ስለሚያልፍ እንዲጠቀምባቸው በማሰብ ነው። ዩኒቨርሲቲ ዘር፣ ብሄር፣ ቀለም ... ሳይለይ የሚያስተናግድ በመሆኑ፤ ሁሉንም ተጠቃሚ ስለሚያደርግ .... በዛ ምክንያት ነው ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልሰጥ የቻልኩት። አሁንም እያደራጀሁ ያለኋቸው መጻሕፍት ስላሉ እንደዚሁ ለሌሎች ተቋማትም እሰጣለሁ። ይህ ብቻም አይደለም። ተቋሙ በከፍተኛ ደረጃ የጥናትና ምርምር ስራዎች የሚሰሩበት ነው። ያበረከትኳቸው መጻሕፍት ደግሞ በይበልጥ ለጥናትና ምርምር ሰዎች በከፍተኛ ደረጃ ሊያግዙ የሚችሉ ናቸው። በተለይ በሕግ፣ ሕገ መንግስት፣ ፍልስፍና .... ባጭሩ ለማህበረሰብ ሳይንስ ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ የሚያግዙ ስለሆነም ነው ዩኒቨርሲቲውን የመረጥኩት።

**አዲስ ዘመን፡- ለፕሬስ ድርጅትስ ምን አስበዋል?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** (ሳቅ) አስቤያለሁ። ይመጣል።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ደረጃ የመጻሕፍት ክምችትዎን በተመለከተ የሚሉን ካለ፤ ማለት እንዴት ነው፤ በተለያዩ ጊዜያት የገዟቸው?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** አዎ፣ የገዛኋቸው ናቸው። የእኔንም ከአባታችን የወረስኳቸውንም አንድ ላይ አድርጌ ነው ስጦታውን ያበረከትኩት።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴ፣ መጻሕፍትን የማሰባሰብና የመለገስ እንቅስቃሴዎች እየታዩ ነው፤ በእንቅስቃሴው ላይ ምን አስተያየት አለዎት?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** አዎ፣ እንደዛ አይነት እንቅስቃሴ እየታየ ነው። በጣም ጥሩ ነው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እያደረገ ያለው መጻሕፍትን አሰባስቦ ለአብርኆት ቤተ-መጻሕፍት የማስረከብ ተግባር ሊያስመሰግነውና ሌሎችም ሊከተሉት የሚገባ አርአያነት ያለው ተግባር ነው። ይህ በሁሉም የአገራችን አካባቢዎች ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ብዬ አስባለሁ። መጻሕፍት ወደ እሚያነቧቸው ጋ መድረስ አለባቸው። አንባቢም የሚያነባቸውን መጻሕፍት በአቅራቢያው ሊያገኝ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ፣ መጻሕፍትን ከመለገስ አኳያ ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** በየግለሰብ ቤት መጻሕፍት በብዛት አሉ። ግሩም የሆነ ኮሌክሽን ያላቸው ሰዎች ሞልተዋል። በመሆኑም ታማኝና የሚረከብ አካል ካለ የሚለግስ ሰው የለም ማለት አይቻልም። ብዙ ይኖራል። ሌሎችም፣ በተለይም ሰፊ የሆነ የመጻሕፍት ክምችት ያላቸው ሰዎች ለተቋማት የመለገሱን ጉዳይ ችላ ሊሉት አይገባም። መጻሕፍትን ለተቋማት መለገስ እውቀትን ለትውልድ እንደማስረከብ ይቆጠራል። ሁሉም ሰው፣ አቅሙ የሚፈቅድ ሁሉ፣ ለመጻሕፍት ልገሳ ጥሪ ፈጣን ምላሽ ሊሰጥ ይገባል። በመሆኑም መጻሕፍት ያላቸው ሰዎች ለተቋማት ቢለግሱ አገርና ህዝብን ጠቀሙ ማለት ነው፤ አንባቢ ትውልድ ከመፍጠር አኳያ የዜግነት ኃላፊነታቸውን ተወጡ ማለት ነው። ትውልድ ስለ ሕግ፣ ሕገመንግስት፣ ፍልስፍና ወዘተ አወቀ ማለት ደግሞ ትርጉሙ ብዙ ሲሆን ጥቅሙም በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ተቋማት የማስተባበሩንና ልገሳውን የመረከቡ ጉዳይ፣ ልክ እንደ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሁሉ፣ ሃላፊነትና ተነሳሽነትን በመውሰድ መስራት ይጠበቅባቸዋል። አሁን እንደሚቻል ታይቷል፤ ሰውም እንደ’ሚለግስ እየታየ ነው። በመሆኑም መጻሕፍትን በማሰባሰብ፣ በመለገስና ተደራሽ በማድረግ ህብረተሰብን ተጠቃሚ ማድረግ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለ ሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ወቅታዊ

# ‹‹አስፈፃሚው አካል ሕግን ማስከበር እና የዜጎችን ደህንነት ማስጠበቅ ዝቅተኛ ግዴታው መሆኑን መረዳት አለበት››

**አቶ ክርስቲያን ታደለ**

**የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ**

**ምህረት ሞገስ**

ባለፈው ሃሙስ የወቅታዊ አምድ ዝግጅታችን ወቅታዊ የአገራችን ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ክርስቲያን ታደለ ጋር ያደረግነውን ቃለምልልስ ይዘን መቅረባችን ይታወሳል። በዛሬው የወቅታዊ አምዳችንም በተለይ የኑሮ ውድነት፣ የሠላም ማጣት እና ከሕወሓት ጋር ባለው ግጭት ዙሪያ የምክር ቤት አባላት ምን እየሠሩ ነው በሚለው እና በሌሎችም አገራዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ከአቶ ክርስቲያን ታደለ ያደረግነውን ቆይታ እንዲህ አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የኑሮ ውድነት እና የሠላም ማጣት ችግሮች የጎሉ እንደሆነ በየጊዜው የምናየው ነው፤ ይህንን ችግር ለማቃለል የምክር ቤቱ ድርሻ ምን ያህል ነው፤ ኃላፊነቱንስ ምን ያህል እየተወጣ ነው?**

**አቶ ክርስቲያን፡-** የኢትዮጵያን የወቅቱን የኑሮ ውድነት የኢኮኖሚ ባለሞያዎች ቢያብራሩት የተሻለ ነበር። ነገር ግን እንደአንድ እንደራሴ ልንገረው የምችለው እኛንም የምክር ቤት አባላት ሁሉ እያሰቃየ ያለ ጉዳይ ነው። መሠረታዊ ፍላጎት ተብለው የተለዩ ዕቃዎች ሳይቀሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዋጋቸው እየጋሸበ ማግኘት እስከማይቻልበት እንደቅንጦት እስከመቆጠር እየደረሱ ነው። ይህንን ችግር ለማቃለልና ለመቅረፍ መንግስት የአጭር ጊዜ የመካከለኛ ጊዜ እና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችን ማቀድ አለበት ብለን እናምናለን።

ባለፈው የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ይህንኑ አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ማብራሪያ ለመስጠት ምክር ቤት ተገኝቶ ነበር። በዛ ወቅት የተነሱ የተለያዩ ጉዳዮች አሉ። በዛ ወቅት የተነሳው በኢትዮጵያ ውስጥ የፖሊሲ እና የቁጥጥር ሥራዎች አለመቀላጠፍ የፈጠሩት ጫና እንደተጠበቀ ሆኖ ዓለም ላይ ያለው ሁኔታም ታሳቢ መደረግ አለበት። በተለይ የዩክሬን እና የሩሲያ ጦርነት ላይ ቀላል አይደለም። መሠረታዊ የሚባለውን የዓለምን የዘይት ፍላጎት 70 በመቶ የሚሆነውን የሚያቀርቡት ዩክሬን እና ሩሲያ ናቸው። ግማሽ የሚሆነውን የስንዴ ፍላጎትንም የሚሸፍኑት እነዚሁ አገራት ነበሩ። ኢትዮጵያ ደግሞ በዋናነት የዘይት ፍላጎቷን የምታስመጣው ከውጪ ነው። አገር ውስጥ ያሉ የዘይት ፋብሪካዎችም የሚያጣሩትን የዘይት ድፍድፍ የሚያመጡት ከእነዚሁ አገራት ነው። ስለዚህ ዘይት በጣም እንዲወደድ ሆኗል። ይህ በዓለም ላይ የተከሰተ ነው። የዘይት ምርታቸውን ወደ ውጪ የሚልኩ እነ ቱርክን የመሳሰሉ አገራትም ወደ ውጪ ከመላክ ታቅበዋል። የፍጆታ ገደብ እስከማስቀመጥ የደረሱም አሉ። የዓለም አቀፍ የንግድ መስመሮችን የባህር ትራንስፖርት ሥርዓቱም ተቃውሷል። ስለዚህ በተቀላጠፈ መልኩ የማጓጓዝ ችግርም ያጋጥማል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ የፀጥታ መደፍረስ ባጋጠመ ጊዜ የትም አገር እንደሚያጋጥመው ከግጭት የማትረፍ እና ሃብት የማጋበስ ሁኔታዎች አሉ። እናም ምርቶችን የማከማቸት አዝማሚያዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው ደግሞ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ምርቶችን ለማስገባት ችግር እንደሚፈጥር ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል።

ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ እና ለፋብሪካ ግብዓት የሚሆኑ ነገሮችን ለማስገባት የሚያስችሉ የውጪ ምንዛሬዎችን አለማግኘት በራሱ ትልቅ ችግር ነው። በዚህ ምክንያት ክፉኛ እየተፈተንን መሆኑን ሁሉም ማወቅ አለበት። ኢትዮጵያ የልጅ ሃብታም ናት። በዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚ ዘርፍ ልምድ እና ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ያላቸው ጉምቱ የሆኑ ኢኮኖሚስቶች ከዚህ ቀውስ ለመውጣት የሚያግዝ አማራጭ ካላቸው ለምክር ቤቱ ሊሆን ይችላል ወይም ለአስፈፃሚው በማቅረብ ህዝባችንን እያሰቃየ ላለው የኢኮኖሚ ህመም ፍቱን ሊሆኑ የሚችሉ የመፍትሔ አማራጮችን እንዲያቀርቡ

**ዳያስፖራው ከምንጊዜውም በላይ ከምንዛሬ እጥረት አንፃር አገር እየተፈተነች መሆኑን በመረዳት ህጋዊ በሆነ መንገድ የውጭ ምንዛሪ በመላክ ቢያንስ ለማስታገስ መተባበር ይኖርበታል**



ጥሪ ማቅረብ እፈልጋለሁ።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያውያን በተለይ ዳያስፖራው ከምንጊዜውም በላይ ከምንዛሬ እጥረት አንፃር አገር እየተፈተነች መሆኑን በመረዳት ህጋዊ በሆነ መንገድ የውጭ ምንዛሪ በመላክ ቢያንስ ለማስታገስ መተባበር ይኖርበታል። ምክር ቤቱም የተለያየ የፓርላማ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት እና ውጪ ጉዳይም ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን በመሥራት ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ በማድረግ መንግስትም የፖሊሲ ማሻሻያ በማድረግ የውጪ ኢንቨስትመንት ሊስቡ እና ሊያሻሽሉ የሚችሉ የገበያ አማራጮችን ምናልባት የውጪ ምንዛሪ ክምችትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት አለበት የሚል እምነት አለኝ።

የውጭ ምንዛሬ ቁጥጥር የሚደረግበት መንገድ የኑሮ ውድነት ላይ ቀጥተኛ የሆነ አስተዋፅኦ አለው። አብዛኛዎቹ የምንጠቀምባቸው የፍጆታ ዕቃዎች በውጪ ምንዛሬዎች የሚመጡ በመሆናቸው እዛ ላይ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል። በእርግጥ እኔ ኢኮኖሚስት አይደለሁም። ነገር ግን በተለይ አስፈፃሚው አካል በዘርፉ ላይ ያሉ ኢኮኖሚስቶች የሚሰጡትን ምክረሃሳብ በወጉ ማድመጥ ይጠበቃል። በዚህ ወቅት ለአገራችን ሁሉም እኩል ያስፈልጋል። ጠቃሚ የሚሆኑ ሃሳቦችን ሙግት እና ክርክር አድርገንባቸው መፍትሔ ሊያመጣ የሚችለው መወሰድ ይኖርበታል። ሕዝባችን በየትኛውም አማራጭ ምርታማነቱን ማሳደግ አለበት። ገበሬው የተገኘውን መሬት ቆፍሮ ቢያንስ የዕለት ፍጆታውን መሸፈን የሚያስችል ምግብ ማምረት ያስፈልጋል። የከተማው ነዋሪ ንግዱ ላይ በደንብ መበርታት ይኖርበታል። መንግስት ደግሞ ነጋዴውን እና አምራቹን ሊደግፉ የሚችሉ አበረታች እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል።

**አዲስ ዘመን፡- ሰላምን በሚመለከትስ ምክር ቤቱ ሚናውን የሚወጣው እንዴት ነው ?**

**አቶ ክርስቲያን፡-** ሰላም በሕይወት ለመኖር ወሳኝ ነው። የኑሮ ውድነቱ ለመባባስ አንደኛው ምክንያት የሠላም እጦት ነው። ሠላም በሌለበት ልማት ሊኖር አይችልም። የውጪም ሆነ የአገር ውስጥ አልሚዎች የፀጥታ መደፍረስ ባለበት አካባቢ አምነው ገንዘባቸውን ሊያፈሱ እና ኢንቨስት ሊያደርጉ አይችሉም። ሰላም ሲኖር ኢንቨስትመንት ይኖራል። ኢንቨስትመንት ሲኖር የሥራ ዕድል ይፈጠራል፤ የቢዝነስ እንቅስቃሴ እና ሌሎችም ብዙ ነገሮች ይኖራሉ። በተለይ የውጭ ኢንቨስተር ሲኖር ደግሞ የውጭ ክምችትን ለማሳደግ አንደኛው አማራጭ ነው። እንደዜጋ ማመን ያለብን ነገር፤ የሕዝባችንን ደህንነት እና አንድነትን ማስጠበቅ በሁለተኛነት ልናስቀምጠው የሚገባ አይደለም። ቀይ መሥመር መሆን መቻል አለበት። ምክር ቤቱ ምንም እንኳ ከተለያየ አካባቢ እና ፓርቲ ተመርጦ የመጣ ቢሆንም የሁሉም ኢትዮጵያውያን ወኪል ነው። የመላው የ120 ሚሊየን ህዝብ ደህንነት ጉዳይ ይገደናል። የኢትዮጵያ አንድነቷ እና ቀጣይነቷ ሊጨንቀን ይገባል። በዚህ ረገድ የምክር ቤቱ እንደራሴዎች በግለሰብ ደረጃም ሠላም ከቤት ስለሚጀምር ከመራጭ ማህበረሰብ ጋር በመውረድ እያንዳንዱ መራጭ ለሠላም በጎ አስተዋፅኦን እንዲያበረክት መቀስቀስ ያስፈልጋል።

ምክር ቤቱ አንዱ ኃላፊነቱ ህግን ማውጣት ነው። ሰላምን፣ ደህንነትን እና ፀጥታን የሚረጋግጡ ሕጎችን ሲያወጣ አስፈፃሚው በወጉ መወጣቱን የመከታተል እና የመደገፍ እና የመቆጣጠር ሥራዎችን እንሠራለን። ለምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ እንባ ጠባቂ ተቋም፣ የሠብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የተወሰኑ የመገናኛ ብዙሃኖች እና የመሣሠሉት ቀጥታ ተጠሪ ናቸው። በዚህ ሒደት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎች ከሌላው ማህረሰብ በተለየ ሕዝቡ ይመለከታቸዋል፤ ይሠማቸዋል። አርአያ አድርጎ ይወስዳቸዋል። ስለዚህ ሠላምን በሚያረጋግጡ

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ



**የኛ ፍላጎት በሒደት መሠል ችግሮች እንዳይደገሙ ራሳቸውን አድሰው ከህዝብ እና ከአገራዊ ፍላጎት አንፃር ብቁ ተቋማት ብቁ አመራር እንዲሆኑ ድጋፍ መስጠት ነው። ድጋፋችን ደግሞ ቁጥጥር ነው።**

ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርብናል።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትልቅ ምክር ቤት ነው። ጥያቄዎች ካሉ በዚህ ምክር ቤት ማናቸውም ጥያቄዎችን ማቅረብ ይቻላል። የሚቀርቡ ጥያቄን ሕዝብ በቀጥታ ይመለከታል። በማናቸውም ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ክርክር ሙግት ማድረግ ይቻላል። ነገር ግን በዋናነት ሁሉም ሕዝብ ለሰላም ዘብ መቆም አለበት። ኢትዮጵያ ስትኖር ብዙ ነገር አለ። ቀልድ ይመስላል። በርካታ አገራት ሲፈራርሱ ታይቷል። ሶሪያ ትልቅ አገር ነበረች። የመን ትልቅ የታሪክ አገር ነበረች። ሊቢያም አደግን ከሚሉ አገሮች በተሻለ መልኩ ዜጎች ተንደላቀው የሚኖሩባት አገር ነበረች። ዛሬ ለዜጎቿ ሲኦል ሆናለች። እንኳን ለመፋቀር እና ለመመካከር ለመጣላትም ለመኮራረፍም አገር ያስፈልጋል። ይህንን በደንብ መረዳት ያስፈልጋል። በሁሉም ነገር ላይ መስማማት ላይኖር ይችላል። በሁሉም ነገር ላይ መስማማት አይጠበቅም። የግድ እንደአገር ለመቀጠል እና በልዩነት ውስጥም ቢሆን በሰላም ወጥቶ ለመግባት አስቻይ ሁኔታን መፍጠር ያስፈልጋል። ለዚህ ዋነኛው ሠላም ነው።

ሠላም ላይ ልዩነት መኖር የለበትም። የተሻለ አማራጭ ፖሊሲ አቅርቦ ነገ በምርጫ ተወዳድሮ ሥልጣን ለመረከብም ሠላም ግዴታ ነው። እኛ እንደእንደራሴዎች በምክር ቤት የሚወጡ ህጎች ለዜጎች ሠላም፣ ደህንነት፣ ፍትህ እና ዴሞክራሲን የሚያረጋግጡ ስለመሆናቸው እናረጋግጣለን። ይሔ ማለት ግን ነገሮች አልጋ በአልጋ ይሆናሉ ማለት አይደለም። ሕዝቡ ይህንን ተረድቶ እኛንም ጭምር መሞገት አለበት። እኛንም የለም የእኛ ፍላጎት እንደዚህ ስለሆነ የምንፈልገው ይህንን ፍላጎታችንን እንድታስፈፅሙልን ነው ብሎ እኛን መጠየቅ መሞገት መቻል አለበት። እያንዳንዱ ሰው ሠላምን የሚረብሹ በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ያሉት ለህግ እንዲቀርቡ ማስቻል አለበት። አስፈፃሚው አካል ሕግን ማስከበር እና የዜጎችን ደህንነት ማስጠበቅ ዝቅተኛ ግዴታው መሆኑን መረዳት አለበት። አንድም ግለሰብ ቢሆን ሊገፋ እና ሊሳደድ አይገባም። እውነት ለመናገር የምናያቸው አዝማሚያዎች ደስ አይሉም። ያሉት ሁኔታዎች ተከባብሮ አንቱ ለመባባል አስቻይ አይደሉም። አገር እየነደደ እና ዜጎች በብሔር እና በሃይማኖት እየተገፋፉ መቀጠል የለባቸውም። ሁላችንም መስከን ይኖርብናል። ነገ በታሪክ ፊት ስለሚኖረን ገፅታ በደንብ ማሰብ አለብን። እኛ ኢትዮጵያውያን ለታሪካችን የምንጨነቅ ነን። ከሞታችን ይልቅ አሟሟታችን የሚያስጨንቀን ለዚህ ነው። ነገ በታሪክ ፊት የኛ ተወላጆች እኛ እንወክለዋለን የምንለው ማህበረሰብ የሚያፍሩብን መሆን የለበትም።

**አዲስ ዘመን፡- ምክር ቤቶች በአብዛኛው ሥራዎችን የሚሠሩት በቋሚ ኮሚቴ ነው። እርሶ የሚመሩት ቋሚ ኮሚቴ ምን እየሠራ ነው?**

**አቶ ክርስቲያን፡-** ጥረቶችን እያደረግን ነው። ዓመታዊ ዕቅድ አለ። ዕቅዳችንን ተከትለን እንሠራለን። እኛ ተልዕኳችን ዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ኦዲት አድርጎ የከፋ የኦዲት ግኝት አለባቸው ያለባቸውን ተቋማት ለይቶ ይልክልናል። ኦዲት ተደራጊ መስሪያቤቶች ብዙ በመሆናቸው ምናልባት ከህዝብ ፍላጎት እና ከሚያንቀሳቅሱት የገንዘብ መጠን አንፃር ምናልባት ለአገር ልማት ከሚያበረክቱት አስተዋፅኦ አንፃር፣ ከሚያንቀሳቅሱት የሰው ሃይል አንፃር እየመዘንን ኦዲት ጉድለቱ አንፃር የከፋ የሚባሉት ላይ ይፋዊ የህዝብ መድረክ እንጠራለን። እስከአሁን በርካታ ተቋማትን አይተናል። በዚህ ዓመትም 26 ተቋማትን ለማየት ዕቅድ ይዘናል። በዕቅዳችን መሠረት እየሔድን ነው። ይፋ መድረክ መያዙ አንድ ነገር ነው። ኦዲት ናሙና ነው። በዚህ ተቋማትም ራሳቸውን እንደመስታወት እንዲያዩበት እንፈልጋለን። ያንን ሊጠሉት አይገባም። መቼም አንድ ሰው አይኑ ላይ ጉድፍ እያለ መስታወት ቢያይ መስታወቱን መጥላት ሳይሆን ጉዱፉን ማንሳት አለበት። የኦዲተርም ሆነ የኛ ሥራ ተቋማት ያለባቸውን ጉድፍ እንዲያነሱ ማድረግ ነው። በህዝብ ዘንድ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ምቹ መደላድል ለመፍጠር ነው። በዚህ ሂደት የአሰራር ክፍተቶች ካሉ እንዲስተካከሉ እና የሕግ ክፍተትም ካለ ለምክር ቤቱ ቀርቦ ጉድለቱን የፈጠረውን አካል ማስተካከል ነው።

የአደረጃጀት እና የአሠራር ችግር ካለም አሠራራቸውን እንዲያስተካክሉ አደረጃጀታቸው ላይ ችግር ካለም አጢነው ከልሰው ለወደፊቱ መሰል ክፍተቶች እንዳይፈጠሩ ማድረግ ነው። እንዝላልነትም ካለ ተጠያቂነት እንዲኖር ነው። ቀጥታ ይወገር ይገደል ማለት ሳይሆን፤ በየደረጃው ተጠያቂነት እንዲዳብር እየሠራን ነው። እስከአሁን ባየናቸው ተቋማት እንዲያስተካክሉ ብለናቸው እነርሱም ማስተካከያዎችን ልከውልን በእርግጥ እያስተካከሉ ነው ወይ የሚለውን በወረቀት ብቻ ሳይሆን በአካልም ሔደን እያረጋገጥን ነው። መሻሻል ያለባቸውም አሉ። ቀጣይነት ያለው ክትትል የምናደርግባቸው አሉ። በተጨማሪ ተጠያቂነት የሠፈነባቸው ተቋማትም አሉ። በክስ ደረጃ ክስ ተመስርቶባቸው ፍርድ ቤት የደረሱ አሉ። በተመሳሳይ ደረጃ በገንዘብ ቅጣት በማስጠንቀቂያ የታለፉም አሉ። አሁን ስላላለቀ እና ይፋ ለማድረግ ስለሚከብድ እንጂ አሁንም ክስ የሚመሠረትባቸው ተቋማት አሉ። የእኛ መሠረታዊ ፍላጎት ግለሰብ አመራሮችን መቅጣት ማስቀጣት አይደለም። የኛ መሠረታዊ ፍላጎት ስህተትን እየነቀሱ እያወጡ ተቋማትን ማኮሰስ አይደለም። አመራሩን ማንቋሸሽ አይደለም። የኛ ፍላጎት በሒደት መሠል ችግሮች እንዳይደገሙ ራሳቸውን አድሰው ከህዝብ እና ከአገራዊ ፍላጎት አንፃር ብቁ ተቋማት ብቁ አመራር እንዲሆኑ ድጋፍ መስጠት ነው። ድጋፋችን ደግሞ ቁጥጥር ነው። ሥራቸውን ሲሠሩ በህግ ተቋማቱ ከተቋቋሙበት ዓላማ አንፃር መሥራታቸውን ማረጋገጥ ነው። ይህንን እየሠራን ነው ብለን እናምናለን። ሌብነትን የሚጠየፉ አመራሮች፣ የመንግስት ሠራተኞች እና ተቋማትን እንፈልጋለን። ምናልባት የከፋ የኦዲት ግኝት ያለባቸው ሹመኞች ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ በሃላፊነት ደረጃ የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖር የለበትም ብለን እናምናለን። ወደ ፊት የክዋኔም ሆነ ሌላ ኦዲታቸው እንደመወዳደሪያ ዶክመንት ተወስዶ በህግ ጭምር እንዲገደብ ጥረት እናደርጋለን። ምክር ቤቱ ይህንን ሲሰራ ነበር። ይመስለኛል ጠቅላይ ሚኒስትሩም ይህንን የምክር ቤቱን ሥራ በበጎ ይቀበሉታል።

**አዲስ ዘመን፡- በምክር ቤቱ ከህግ ውጪ የሚፀድቁ ህጎችን በሚመለከት የመገናኛ ብዙሃን ቦርድን በሚመለከት ሃሳብ አቅርበው ነበር። እንዲህ አይነት ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በህግ መጠየቅ የሚቻልበት መንገድ የለም?**

**አቶ ክርስቲያን፡-** አለ። ምክር ቤቱ የሚመራበት የአባላት የአሰራር ደንብ አለ። በደንቡ ላይ በየትኛው ደረጃ በምክር ቤቱ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ድጋሚ አይታዩም። ነገር ግን በልዩ ሁኔታ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሰራር እና የአባላት የሥነምግባር ደንብ አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የተቀመጠ አለ። ግልፅ የሆነ የህግ ሥህተት ካለ በዛው ደንብ በአንቀፅ 49 ንዑስ 3 ላይ የተቀመጠ እና በልዩ ሁኔታ በአማካሪ ታይቶ የተወሰነው ውሳኔ የሕግ ስህተት ስላለበት ማሻሻል ይቻላል የሚል ግልፅ አሠራር አለ። ስለዚህ በባለፈውም የኢትዮጵያ ብሮድካስት የመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን የቦርድ አመራሮች ሹመት ሲፈፀም በአዋጅ የተቀመጠው 1238/2013 ያስቀመጣቸው አሠራሮች እና ሥነስርዓቶች አልተከበሩም። በወቅቱ በምክር ቤቱ እኔም ዕድሉን አግኝቼ ስለነበረ ይህ ነገር የስነስርዓት እና የህግ ጥሰት ስለመሆኑ ጠቅሼ ነበር። እኔ የምወስደው በበጎ ነው። አዋጁ ላይ ግንዛቤ ባለመኖሩ ነው። ድምፅ ተሰጥቶ ፀድቋል። ነገር ግን አሠራሩም የሚፈቅድ በመሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ በቀጣይ በሚኖረን የምክር ቤት ስብሰባ ይህን ጉዳይ አንስተነው ይታያል የሚል ተስፋ አለኝ።

እኔ ምክር ቤት የገባሁት የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄን ወክዬ ነው። እዚህ የፓርቲያችን የፓርላማ ቡድን አለ። በፓርቲ ተጠሪያችን በኩል እንዲያዝ ተደርጓል። ምክንያቱም መነጋገሪያ ሆኗል። የሚዲያው የዜጎች እና የፖለቲከኞች መነጋገሪያ ሆኗል። ነገር ግን ይህ ወደ ፊትም ሊፈጠር ይችላል። ዋናው ነገር ጉዳዩ ከታወቀ በኋላ ትክክለኛውን ህጋዊውን መንገድ ሥርዓት ማስያዝ ከእኛ የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። ይህንን ማድረጋችን ለምክር ቤቱ ሞገስ እና ክብር ቢሰጠው እንጂ ምክር ቤቱን የሚያኮስስ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- ከሕወሓት ጋር ባለው ግጭት ላይ በምክር ቤቱ ምን መደረግ አለበት ብለው ያምናሉ?**


**አቶ ክርስቲያን፡-** በዚህ ጉዳይ ላይ አፈ ጉባኤው ቢጠየቁ መልካም ነበር። ነገር ግን እንደአንድ የምክር ቤት አባል እንደግለሰብ አስተያየቴን ስሰጥ የምክር ቤቱ አቋም ተደርጎ መወሰድ የለበትም። በመሠረቱ ሰላም ከምንም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው። የትኛውም አካል በኢትዮጵያ ላይ በጎ አበርክቶ ሊኖረው ይችላል። አሁንም ድረስ ሕወሓት ባዘጋጃቸው ደንቦች እየተመራን ነው። በአካል ጫካ ቢሆንም በአሠራር እና በስሪት ቤተ መንግስት ያለ ቡድን ነው። የምንመራበትን የአባላት ደንብ ሕገመንግስቱም ሁሉም በሕወሓት የተዘጋጀ ነው። ግለሰቦቹ በአካል ባይኖሩም ሥርዓት እና ሥሪቱ የሕወሓት ነው። ይሔ አንድ ራሱን የቻለ ክርክር የሚፈልግ ነው። ነገር ግን እኔ መናገር የምፈልገው በመርህ ነው። ሕወሓት በዚህ ምክር ቤት አሸባሪ ተብሎ የተፈረጀ ነው። በሌላ በኩል አሁን ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ይታወቃል። ሕወሓት እንደ ድርጅት ኢትዮጵያን ለማፍረስ ገሃነም ድረስ እገባለሁ ብሎ የተነሳ ነው። ዛሬም ድረስ የአፋር እና የአማራን ግዛቶችን ተቆጣጥሮ የሚገኝ አካል ነው። ዛሬም ድረስ አፈንግጦ ከኢትዮጵያ ጋር ውጊያ እየፈፀመ ነው። ለሰላም በጎ እርምጃ እየወሰደ አይደለም። ያከማቸውን ሃብት በመጠቀም ከኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም በተቃርኖ የቆመ አካል ነው። ስለዚህ በኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም ላይ የመጣ ነው።

የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚመለከተው ኢትዮጵያውያንን ነው የሚል እምነት አለኝ። ኢትዮጵያ ካለችበት ችግር እንዴት ትውጣ በሚል ማሳተፍ መርዝ ቀማሚን ባለመድሃኒት የማድረግ ስህተት ውስጥ እንዳይገባ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ግን ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ሕዝባችን ነው። የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያ እዚህ እንድትደርስ ጉልህ አበርክቶ ያለው ሕዝብ ነው። ይህንን እንዲቀጥል። ኢትዮጵያን ወደ ፊት በማሻገር ሒደት ውስጥ የሚሳተፍበት ፕላት ፎርም መዘጋጀት እንዳለበት አምናለሁ። ፕላት ፎርሙ እንዴት መደረግ አለበት በሚለው ላይ ምክክር ያስፈልጋል። ቀጣይ ንግግር ያስፈልጋል። በየትኛውም ሁኔታ ደግሞ ሰላም እንዲሰፍን እንፈልጋለን። በትግራይም ሆነ በአፋር እና በአማራ ክልል በየትኛውም አካባቢ ሰላም እንዲሰፍን እንፈልጋለን። ሁሉም ባለድርሻ አካል መወያየት መመካከር አለበት። ምናልባት ኢትዮጵያን ሰላም ለማድረግ የሚወሰነው ውሳኔ የሚጎመዝዝ ቢሆን እንኳ ሕዝብን ወደፊት የሚያሻግር እስከሆነ ድረስ መቀበል አለብን። በተለይ የፖለቲካ ሃይሎች በእነርሱ እምነት ኢትዮጵያን ሰላም ሊያደርግ የሚችል ዕቅድ ቢያቀርቡ ልንነጋገርበት የምንችልበት ዕድል አለ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ**

**አቶ ክርስቲያን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ስፖርት



## የተሻሻለው የስፖርት ማህበራት መመሪያ የስፖርት ችግርን ለመቅረፍ

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ ስፖርት በሚጠበቀውና በሚፈለገው ልክ ላለማደጉ በርካታ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል። ከእነዚህ መካከል ግን መንግስታዊ የሆነው የስፖርት ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር ቀዳሚው ነው። በመሆኑም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የተሰጠውን ኃላፊነት መሰረት በማድረግ ሲሰራበት የቆየውን አገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት መመሪያ አሻሽሏል።

ሚኒስቴሩ የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 37 1/ነ/ በተሰጠው ስልጣን፤ የስፖርት ማህበራቱን መመሪያ የማውጣት፣ የመመዝገብ፣ ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለው። በዚህም መሰረት በብሄራዊ የስፖርት ሪፎርሙ እንዲሁም ስለስፖርት ባለሙያዎች በተመላከተው መሰረት መመሪያውን በማሻሻል ወደ ተግባር መቀየሩን አስታውቋል።

ተሻሽሎ የቀረበው ይህ መመሪያ ከመጽደቁ አስቀድሞ በተለያዩ የስፖርት ባለድርሻ አካላት ይፋ በማድረግና በማወያየት በሂደት እንዲዳብር ተደርጎ ነው። የስፖርት ማህበራት ማቋቋሚያ መመሪያ ባለፈው የካቲት ወር መጨረሻ 2014 ዓ.ም ጸድቆ ለሚመለከታቸው አካላት መሰራጨቱንም ሚኒስትሩ በመግለጫው ጠቁሟል።

የስፖርቱን መሰረታዊ ችግር ለመቅረፍ ግማሽ መንገድ ይጓዛል የተባለለት መመሪያው፣ ተፈጻሚ የሚሆነውም በአገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት፣ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ እና ፓራሊምፒክ ኮሚቴዎች ላይ ነው። የደንቡ



አስፈላጊነት፤ በዋናነት ከዚህ ቀደም የስፖርት ማህበራቱ አሰራርና አደረጃጀት ጥያቄ የሚያስነሳ ስለነበረ ነው። በመመሪያው አለመኖር ምክንያትም በምንም ዓይነት ሁኔታ ለሚፈጸም ጥፋት ተጠያቂነት ባለመኖሩ መመሪያው እንዲሻሻል ተደርጓል። መመሪያው ከዓለም አቀፍ ተቋማት ልምድ እንዲሁም ከአገሪቷ ህግ አንጻር ተቀምሮ የተዘጋጀም ነው።

መመሪያው ትኩረቱን ካደረገባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የፈቃድ አሰጣጥ ሲሆን፤ ሲሰራበት በቆየው ደንብና መመሪያ ውስጥ ያልነበረ አሰራር መሆኑ ታውቋል። ይኸውም የስፖርት ማህበራት እንዲያሟሉ የተቀመጠላቸውን መስፈርቶች በማሟላት ምዝገባ መፈጸም ነው። ከመስፈርቶቹ መካከልም በማህበራቱ ስር የሚገኙ የስፖርት ክለቦች ስያሜ፣ አርማ እና መዝሙሮች ከብሄር፣ ፖለቲካና ሃይማኖት ጋር የተያያዙ እንዳይሆኑ የሚያሳስብ ነው።

የፈቃድ እድሳቱ በየአራት ዓመቱ የሚደረግ ሲሆን፤ በሚቀጥሉት ሶስት ወራት እንዲጠናቀቅም እየተሰራ ይገኛል። ነገር ግን መስፈርቱን ያላሟሉ የስፖርት ማህበራት አራት ዓመት የማደራጃ ጊዜ ይሰጣቸዋል። ይህም ሆኖ መስፈርቱ መሟላት ካልቻለ ግን ማህበራቱ አገር አቀፍ ዕውቅና ማግኘት የማይችሉ በመሆኑ የክልል አሊያም ከተማ አስተዳደር ደረጃ ይቆያሉ።

አገር አቀፍ የስፖርት ማህበራቱ በተሻሻለው መመሪያ መሰረት ከመንግስት የሚያገኙት የፋይናንስ ድጋፍ እንዲሁም የንብረት አጠቃቀም ኦዲት እንደሚደረግም ተመላክቷል። ከአቻ ተቋማት ጋር የሚኖራቸው ዓለም አቀፍ ግንኙነታቸውን እንዲሁም ማህበራቱን የሚመሩት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስልጣንና የስራ ዘመን ላይም ሊሆኑ ይገባቸዋል ያላቸውን መመሪያው በግልጽ አስቀምጧል።

በአንጻሩ ማህበራቱ ዕውቅና እና እድሳት ሳያደርጉ ውድድሮችን ማካሄድ፣ በስራቸው የሚገኙ ክለቦች ስያሜ፣ አርማ እንዲሁም መዝሙር የብሄር፣ ሃይማኖትና ከሌሎች ፖለቲካዊ ጉዳዮች ነጻ ካልሆነ፣ በስፖርት ስም በሚደረጉ ተገቢ ያልሆኑ የውጪ ጉዞዎች ላይ፣... ክልከላ አድርጓል።

የተሻሻለውን መመሪያ ተከትሎም የኢፌዴሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ቀጄላ መርዳሳ፤ የተሻሻለ መመሪያ የዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበራት ህግ ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ የተደነገገ መሆኑን ገልጸዋል። የዓለም አቀፉን ኦሊምፒክ ኮሚቴ ጨምሮ ማህበራቱን በሚመጥን ደረጃ የስፖርት አደረጃጀቱ እንዲከናወን የሚያደርግና የተናበበ መሆኑንም ነው ያስታወቁት። ከዚህም ባለፈ ማህበራቱ ስፖርቱን በመላ ሃገሪቷ እንዲያስፋፉና ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ የሚያደርግም ነው ብለዋል።

በኢፌዴሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት በበኩላቸው፤ ማህበራቱ በርካታ ችግሮች እንዳሉባቸው ጠቁመዋል። በርካታ አገር አቀፍ ማህበራት ትልልቅ ስያሜ እያላቸው ነገር ግን በሚመጥናቸው አደረጃጀት ያልነበሩበት፣ የስፖርት ስራ አስፈጻሚዎች ከተመረጡ በኋላ አለመውረድ፣ በዚህም ተጠያቂ የማይሆኑበት እንዲሁም ቡድን ከፍለው እርስ በእርስ ልዩነት የሚፈጥሩበት እንደነበር አብራርተዋል። በመሆኑም የተሻሻለውን መመሪያ ወደ ተግባር ከመለወጥ አንጻር ሚኒስቴሩ ያለውን ቁርጠኝነትም አረጋግጠዋል።

## የአልሙኒየም በሮች እና መስኮቶች አቅርቦት እና ገጠማ ሥራ ጨረታ

ድርጅታችን ሀገረሰብ ሪል እስቴት አ.ማ ለሚያስገነባው 2B+G+15 ቅይጥ ሕንፃ ግንባታ ከታች በሰንጠረዥ በቀረበው መልኩ የሚፈለገውን ዕቃ አቅርበው ሥራውን የሚሠሩ ድርጅቶችን አወዳድሮ ማሠራት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ሥራውን ለመሥራት ሕጋዊ ፍቃድ (የታደሰ ንግድ ፍቃድ ፣ የቫት ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የገቢዎች ክሊራንስ) እና አቅሙ ያለው ድርጅት የጨረታ ሰነዱን ሪቼ አካባቢ ከሚገኘው ቢሯችን የማይመለስ ብር 500 በመክፈል መውሰድ ይችላል፡፡ ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በሚቆጠሩ አስር ቀናት ውስጥ መመለስ ይኖርበታል፡፡ ጨረታው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የሚከፈት ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት እና ስፋት | ለመወዳደር የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች |
|---|---|---|
| 1 | 1,130 ካሬ የአልሙኒየም በር እና መስኮት አቅርቦት እና ገጠማ | ❖ የሚቀርበው የአልሙኒየም ፕሮፋይል ጥቁር ከለር ያለው ሆኖ አኖዳይዝድ፣ ማት እና ውፍረቱ 1.6ሚሊ.ም (1.6mm Black, Matte & Anodized) መሆን ይኖርበታል፤<br>❖ መስታወቱ፡ 5mm clear glass መሆን ይኖርበታል፤<br>❖ ተጫራቹ የሚሰራበትን (ዋጋ የሰጠበትን) የአልሙኒየም ፕሮፋይል ሳምፕል ከጨረታ ሰነዱ ጋር አብሮ ማስገባት ይኖርበታል፤<br>❖ ተጫራቹ ለሥራው የሚያስፈልገው ያህል በቂ አልሙኒየም እና መስታወት በእጁ ያለ (Sufficient available Stock) እና በ 1ወር ጊዜ ውስጥ ሠርቶ ማስረከብ የሚችል መሆን ይኖርበታል፤<br>❖ ተጫራቹ የጨረታ ማስከበሪያ 50,000 ብር ሲ.ፒ.ኦ በአሰሪው ድርጅት ስም ማለትም HAGERESEB REAL ESTATE S.C አሠርቶ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማስገባት ይኖርበታል፤<br>❖ ተጫራቹ የሚጫረትበትን በር እና መስኮቶች ዲዛይን (Schedule) ከጨረታ ሰነዱ ጋር መውሰድ ይኖርበታል፤ |

አድራሻ፡- ከጨርቆስ ወደ ሪቼ በሚያስወጣው መንገድ ከማንዴላ የርቀት ትምህርት ዝቅ ብሎ ወረዳ 10 ጋር ሳይደርስ ዞዊ መካከለኛ ክሊኒክ አጠገብ፡፡
ስልክ ቁጥር፡- 0930 601161፣ 0114 701360

### ሀገረሰብ ሪል እስቴት አክሲዮን ማህበር

## የመስኮት ደፍ (Window Sill) ግዥ ጨረታ

ድርጅታችን ሀገረሰብ ሪል እስቴት አ.ማ ለሚያስገነባው 2B+G+15 ቅይጥ ሕንፃ ግንባታ ከታች በሰንጠረዥ በቀረበው መልኩ የመስኮት ደፍ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ዕቃውን ለመሸጥ ሕጋዊ ፍቃድ (የታደሰ ንግድ ፍቃድ፣ የቫት ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የገቢዎች ክሊራንስ) እና አቅሙ ያለው ድርጅት የጨረታ ሰነዱን ሪቼ አካባቢ ከሚገኘው ቢሯችን የማይመለስ ብር 500 በመክፈል መውሰድ ይችላል፡፡ ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በሚቆጠሩ አስር ቀናት ውስጥ መመለስ ይኖርበታል፡፡ ጨረታው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የሚከፈት ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት እና ስፋት | ለመወዳደር የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች |
|---|---|---|
| 1 | 68.21 ካሬ Window Sill (የመስኮት ደፍ) አቅርቦት | ❖ የሚቀርበው የመስኮት ደፍ፡ ጥቁር ከለር ያለው እና ውፍረቱ 3 ሳንቲም የሆነ ቡርኖስ እና ግሩቭ የተሠራለት እምነበረድ (3cm thick Black Marble) መሆን ይኖርበታል፤<br>❖ ተጫራቹ የሚሠራበትን (ዋጋ የሰጠበትን) የመስኮት ደፍ ሳምፕል ከጨረታ ሰነዱ ጋር አብሮ ማስገባት ይኖርበታል፤<br>❖ ተጫራቹ ለሥራው የሚያስፈልገው ያህል በቂ የመስኮት ደፍ በእጁ ያለ (Sufficient available stock) እና በ1ወር ጊዜ ውስጥ ሠርቶ ማስረከብ የሚችል መሆን ይኖርበታል፤<br>❖ ተጫራቹ የጨረታ ማስከበሪያ 10,000 ብር ሲ.ፒ.ኦ በአሠሪው ድርጅት ስም ማለትም HAGERESEB REAL ESTATE S.C አሠርቶ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማስገባት ይኖርበታል፤<br>❖ ተጫራቾ የሚጫረትበትን የመስኮት ደፍ ልኬት ዝርዝር (Schedule) ከጨረታ ሰነዱ ጋር መውሰድ ይኖርበታል፤ |

አድራሻ፡- ከጨርቆስ ወደ ሪቼ በሚያስወጣው መንገድ ከማንዴላ የርቀት ትምህርት ዝቅ ብሎ ወረዳ 10 ጋር ሳይደርስ ዞዊ መካከለኛ ክሊኒክ አጠገብ፡፡
ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር፡- 0930 601161 ፣ 0114 701360

### ሀገረሰብ ሪል እስቴት አክሲዮን ማህበር